Join our official telegram Channel for more
@AmharicSpritualBooks

# አሥርቱ ትእዛዛትና የዘመኑ የሞራል ውድቀት

ዶክተር መለሰ ወጉ

እግዚአብሔር እኔንና እናንተን የሚያስደንቅ አዕምሮ ሰጥቶን ፈጠረን እንጂ፣ ማሰብ እንደማይችል በባትሪ ድንጋይ እንደሚሠራ አሻንጉሊት (ሮቦት) አድርጎ አልፈጠረንም። ማመዛዘን፣ መምረጥ እንድንችል ጥሩ አዕምሮ ሰጥቶናል። አዕምሯችን የታደሰና የተለወጠ (ሮሜ 12፥2) ቢሆንም፣ በቀላሉ የመሳሳት ዝንባሌ ያለው ነው። ይህንን የሚያውቀው እግዚአብሔር ሊያግዘን ስለፈለገ፣ ከመስመር እንዳንወጣ "ሕግን" ሰጠን። እንደምናውቀው "አሥርቱ ትዕዛዛት" ለጥያቄያችን ሁሉ መልስ ባይሰጠንም፣ ለውሳኔ የሚረዳን መመሪያ ይሆንልናል። ስለዚህ "የእግዚአብሔርን ሕግ ትቼ በራሴ ሕግ እመራለሁ" ማለት ከጉዳት በስተቀር ጥቅም የለውም። የሕግን ጠቃሚነትና አስፈላጊነትን የሚያውቀው ኢየሱስ፣ *"ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም… ማንም ከእነዚህ ትእዛዛት አነስተኛዪቱን እንኳን ቢተላለፍ፣ ሌሎችንም እንዲተላለፉ ቢያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን እነዚህን ትእዛዛት እየፈጸመ ሌሎችም እንዲፈጽሙ የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይባላል"* (ማቴ. 5፥17, 19) አለ። ይህን የኢየሱስን ቃል ስንሰማ፣ ክርስቲያኖች ሕግን ለመጠበቅም ሆነ ላለመጠበቅ ምርጫ እንደሌለን እንገነዘባለን። ደስ ካለን፣ ምርጫችን ከሆነ ብቻ የምንጠብቀው አይደለም።

አሥርቱ ትዕዛዛት ጊዜ ያለፈበት፣ አሁን ባለንበት በጸጋ ዘመን የማያስፈልግ የሚመስላቸው ክርስቲያኖች አሉ። *"በጸጋ"* ዘመን ሕግ የማያስፈልግ ይምሰላቸው እንጂ፣ የእግዚአብሔር ሕግ በአዲስ ኪዳን ዘመን ውስጥ ላለነውም ክርስቲያኖች መልካም ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ "አሥርቱ ትዕዛዛትን" ሲሰጥ ከፍቅር የተነሳ እንጂ፣ ሸክም ሊጭንባቸው፣ በእነርሱ ላይ ያለውን ሥልጣን ሊያሳይበት አይደለም። እነዚህ አሥርቱ ትዕዛዛት በሙሴ ዘመን የነበሩት እስራኤላውያንን ብቻ ሳይሆን፣ ሁላችንንም ይመለከታል። በባሕሪያችን እግዚአብሔርን መምሰላችንን እንድናይበት የተሰጠን መስታወት ነው። በምንወስደው እያንዳንዱ እርምጃ ለተጠራንበት ታማኞች እንድንሆን፣ በፍጹም ልባችን፣ በፍጹም ኃይላችን እግዚአብሔርንና ጎረቤታችንን እንድንወድ ያስችለናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ በእያንዳንዱ ትእዛዝ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዳለ ለማሳየት ሞክረናል።

ደህንነት ልቡን ለክርስቶስ በእምነት ለሰጠ ለማንኛውም ሰው በነጻ የሚሰጥ ስጦታ እንጂ፣ ሕግን በመጠበቅ የሚገኝ እንዳልሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ይሁን እንጂ፣ እንደ ፈለግን እንድንኖር፣ ደስ ያለንን ሁሉ እንድናደርግ፣ "በእኛ ሕይወት ውስጥ ሥልጣን ያለው ማንም የለም" ብለን እንደፈለግነው እንድንኖር ሙሉ ፈቃድ አልተሰጠንም። የባሕሪያችን ሞዴል በከፊል ብሉይ ኪዳን ባስተማረው ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው። በአዲስ ኪዳንም ሕግ ያለውን ከፍተኛ ሥፍራ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፣ *"ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዙም ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው"* (ሮሜ 7፥12) ይላል።



በአዲስ ኪዳን ዘመን "ከጸጋ" በታች በመሆናቸው፣ ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ ለመኖር ፈቃድ ያገኙ፣ እግዚአብሔር ከእነርሱ ቅድስናን የማይጠብቅ መስሎ የሚሰማቸው አሉ። ሃይማኖት በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም የበለጠ እያደገና እየተጠናከረ ነው፤ ለአምልኮት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት ሰዎች ቁጥር እየጨመረ፣ የክርስቲያኖች የቅድስና ሕይወት ግን ወደታች እያቆለቆለ ነው። በግል ሕይወታቸው ውስጥ የክርስቶስ ማንነትና ውበት አይታይም። አንዳንድ ክርስቲያኖች *"እስካልተያዝኩ ድረስ እሰርቃለሁ…በማንም ሰው ሕይወት ላይ ጉዳት እስካላመጣሁ ድረስ፣ ለበጎ እስከተጠቀምኩበት ድረስ ብዋሽ ምንም አይደለም…ከተረፈው ባለጸጋ፣ የተወሰደበት መሆኑ ከማይሰማው ሰው ብሰርቅ፣ ብነጥቅ ምንም አይደለም…መንግሥት ሰቀረጥ ከሚበላው፣ መንገድ ፈልጌ እኔው ራሴ ልብላው…"* በማለት የራሳቸውን ሕግ ያወጡ ይመስላሉ። በዚህ ዓይነት የክርስቲያኖች *"የሞራል ውድቀት"* ከምንጊዜውም የበለጠ እንደ አሁኑ ዘመን ጎልቶ የታየበት ጊዜ የለም። ይሄም መጽሐፍ ተዘጋጅቶ የቀረበው፣ በዚህ ነጥብ ላይ አስፈላጊ የሆነውን ትምህርት በመጠኑም ቢሆን ለመስጠት ነው።

ሰዎች በአንድ በኩል እግዚአብሔርን እየፈለጉት፣ በሌላው በኩል ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ሕግ ግድ የማይኖራቸው፣ በትዕዛዙ መሠረት ለመኖር የማይፈልጉበት ምክንያት ምን ይሆን? ለዚህ ጥያቄ ጥሩ መልስ ይሆናል ብለን የምናስበው፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጸው ሰዎች እግዚአብሔርን በትክክል ስለማያውቁት ነው። ቢያውቁት ኖሮ ሕጉ ያለውን ሙሉ ሥልጣን ይረዱ ነበር። እግዚአብሔርን በትክክል ካወቅነው፣ ሕጉንም ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ እናከብረዋለን። "የመናኝ ጉዞ" የሚለውን መጽሐፍ የጻፈው ዮሐንስ ቡንያን የተባለው ጻድቅ ሰው፦

> "ሕግን እንደሚገባው የማይረዳ፣ የኃጢአትን ባሕሪ ማወቅ አይሆንለትም። የኃጢአትን ባሕሪ ካላወቀ ደግሞ የአዳኙን ባሕሪ መረዳት አይችልም" አለ።

አሥርቱ ትዕዛዛት በእግዚአብሔር ቅድስና ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፣ ዛሬም በአማኞች ሕይወት ውስጥ መኖር አለበት። ኢሳያስ፣ *"እግዚአብሔር ስለ ጽድቁ ሲል፣ ሕጉን ታላቅና የተከበረ በማድረግ ደስ አለው"* ይላል (ኢ.ሳ. 42፥21)። ጳውሎስም እግዚአብሔር የሰጠው ትዕዛዝ (ሕግ) በአማኞች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ሊሰጠው እንዲሚገባ ደጋግሞ ገልጿል። *"ታዲያ እንዲህ ከሆነ ከእምነት የተነሣ ሕግን ዋጋ የሌለው እናደርግ ይሆን? ፈጽሞ አይደረግም፤ ሕጉን እናጸናለን"* ይላል (ሮሜ 3፥31)። ዝቅ ብሎ፣ *"…ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዙም ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው"* ይላል (ሮሜ 7:12)።

ይህ መጽሐፍ፣ ቀደም ሲል በካሴት አዘጋጅተን ካወጣነው ትምህርት ላይ የተወሰደ ሲሆን፣ በጣም ወቅታዊ የሆነ ትምህርት ያዘለ ነው። የክርስቲያኖች

የቅድስና ጉድለት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመምጣቱ፣ ክርስቲያኖችን የማስ ጠንቀቅና የማሳሰብ ኃላፊነታችንን ለመወጣት በተለያየ አርዕስትና መንገድ አስፈላጊውን ትምህርት በየጊዜው መስጠታችንን ብዙዎቻችሁ ትረዳላችሁ። የዚህም መጽሐፍ ዋና ዓላማ ከዚሁ የተለየ አይደለም። ይህ ትምህርት በቀላሉ በብዙዎች እጅ እንዲገባና ብዙዎች እንዲጠቀሙበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ዓላማ፣ አንባቢዎችን የትምህርተ መለኮት (የቲዮሎጂ) ምሁር (ሊቅ) እንዲሆኑ ለማድረግ አይደለም። ይህን ለማድረግ ፈቃዱ ቢኖረን እንኳን ችሎታው የለንም። ዓላማችን ስለ "አሥርቱ ትዕዛዛት" መጠነኛ ሀሳብ ለመስጠት፣ እንዲሁም በወንጌሉ ውስጥ ያለውን እውነት በሕጉ ውስጥ ማየት እንድንችል ትምህርት ለመስጠት ነው። ይህን መጽሐፍ ስታነቡ እግዚአብሔር በቂ የሆነ መረዳትን እንዲሰጣችሁ ምኞታችንና ጸሎታችን ነው። በመጨረሻ አገልግሎታችንን በታማኝነት ለረጅም ጊዜ ለደገፋችሁ ሁሉ ምስጋናችንን ከልብ እናቀርባለን። የሁላችንም የአገልግሎት ተሳትፎ የተለያየ ይሁን እንጂ፣ በመጨረሻው ቀን ከጌታ የምንቀበለው ሽልማታችን ግን እኩል ነው።

መሰሰ ወጉ



# ምዕራፍ አንድ

# ሕግ እንዴት መኖር እንዳለብን ይመራናል

"እምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ኃይልህ ውደድ።
ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዛት በልብህ ያዝ።
ለልጆችህም አስጠናቸው፤ በቤትህ ስትቀመጥ፣ በመንገድህም
ስትሄድ፣ ስትተኛና ስትነሣም ስለ እነርሱ ተናገር። በእጅህ ላይ
ምልክት አድርገህ እሠራቸው፤ በግንባርህም ላይ ይሁን።
በቤትህ መቃኖች በግቢህም በሮች ላይ ጻፋቸው" (ዘዳ. 6፥5-9)።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዝቆ የማያልቅ ብዙ ትምህርቶች እያሉ ስለ አሥርቱ ትዕዛዛት በስፋውና በጥልቀት ለማስተማር የተነሳሁበት ምክንያት አንዳንዶቻችሁን ሳይደንቃችሁ እንደማይቀር እገምታለሁ። ከዚህ በፊት አዘጋጅቼ ሳቀረብኩላችሁ ትምህርቶች ሁሉ ምክንያት ነበረኝ። ልክ እንደ ሌሎቹ ይህንንም ትምህርት አዘጋጅቼ ያቀረብኩበት ምክንያት አለኝ። ትልቁና ዋናው ምክንያቱ ስለ አስርቱ ትዕዛዛት የትምሕርተ መለኮት ዕውቀት እንዲኖራችሁ በማለብ ሳይሆን፣ በክርስቲያኖች መካከል በአሁኑ ዘመን ጎልቶ የሚታየውን የሞራል ውድቀት፣ ስለ ቅድስና ሕይወት ያለውን የግዴለሽነት ሕይወት በማየት በዚህ አቅጣጫ ሰፋ ያለ ትምሕርት ለመስ

ጠት ነው። ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወቅታዊና የሰዎችን ሕይወት በቀጥታ ሊነካ የሚችለውን ትምህርት እንዲሰጠኝ እግዚአብሔርን ከመጠየቅ በቀር አማኞችን የሚያስደስታቸውን ትምህርት በመፈለግ ጊዜ አላባክንም። የሰዎችንየግል ሕይወት የማይነካ፣ ተራ ፍልስፍና፣ ሀሳብ ብቻ የሆነ፣ ተጨባጭነት የሌለው ወይም በተግባር ላይ የማይውል የረቀቀ ትምሕርተ መለኮት ማቅረብ አልፈልግም። መንፈስ ቅዱስ የጊዜውን ሁኔታ እንዳይ ዓይኖቼን እንዲከፍትልኝ ሁልጊዜ እጸልያለሁ። የራሴንም ጊዜ ሆነ አዘጋጆቼ የማቀርበውን ጽሁፍ የሚያነቡትን ሰዎች ጊዜ በከንቱ እንዳላጠፋ፣ ያላሳከካቸውን ቦታ አካለሁ ብዬ በማከክ እንዳልጎዳ፣ የተቻለኝን ያህል እጠነቀቃለሁ።

መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም የሚነካ መልዕክት እንዲሰጠኝ ከልቤ መጸለይ ቅድሚያ የምሰጠው አገልግሎቴ ነው። ከዚህ በፊት አዘጋጆቼ ባቀረብኳቸው መልዕክቶች፣ የመንፈስ ቅዱስ አሳብና ምሪት ያለበት መሆኑን የምረዳው፣ ከተለያየ ሥፍራ መልዕክቱን የሰሙ ሰዎች፣ “ይሄ መልዕክት ለእኔ ብቻ ሰትል ያዘጋጀኸው ይመስላል” የሚሉኝን የተለያዩ ሰዎች አስተያየት ከተለያየ ስፍራ ስሰማ ነው። ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው አንድ ነገር ቢኖር፣ “እነከሌን ያስደስታል” ወይም “እነከሌን ቅር ያሰኛል” ብዬ እየመረጥኩ የማላቀርብላችሁ፣ ወይም ማቅረብ ያለብኝን ሰውን በመፍራት ብቻ ወደ ኋላ የማልል መሆኑን ነው። “ይመለከተኛል” የሚለው ለመጠቀም፣ “አይመለከተኝም” የሚለው ደግሞ ችላ ብሎ ለማለፍ፣ ሁሉም የራሱ የሆነ ነጻነት እንዳለው አውቃለሁ።

“አሥርቱ ትዕዛዛት” የሚለውን ቃል ስንሰማ፣ መጀመሪያ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ምን ይሆን? የሚታየን፣ በድንጋይ ላይ የተቀረጸ ሕግ፣ በሙሴ ዘመን ለነበሩ ሰዎች የተሰጠ፣ በአሁኑ ዘመን ካለነው ክርስቲያን አማኞች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው ሆኖ ይሆን? “ከአሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያሳየው የትኛው ክፍል ነው? ኢየሱስ የሰበከውንና ያስተማረውን የነጻነት መልዕክት አይቃረንም ወይ?” በማለት እንጠይቅ ይሆን? አሥርቱ ትዕዛዛት ምንጩ፣ በጣም ከሚወደን፣ ነጻነታችንን ከሚያከብር አምላክ የመጣ መሆኑን ምናልባት ለአንዳንዶቻችን በግልጽ ላይታየን ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር አሥርቱ ትዕዛዛትን የሰጠን ለጥቅማችን ብሎ ነው። የሚያሳዝነው፣ አሥርቱ ትዕዛዛትን በአግባቡ ባለመያዛችን፣ እርሱ ከሚፈቅደው ክልል በመውጣት፣



የራሳችንን ፈቃድና ፍላጎት በመከተል በአንዳንድ ነገር ተጠላልፈን ጉዳት ላይ መውደቃችን ነው። ስሜታዊ የሆነውን ነገር በመከተል፣ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለጥቅማችን ብሎ በሰጠን አሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ማየት ያቅተን መሆናችን ያሳዝናል። አሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ስምንቱ የቀረቡት በአሉታ ነው። ይኸውም፥ “አትግደል…አታመንዝር… አትስረቅ… በሀሰት አትመስክር… አትመኝ… አታምልክ… አይነርሀ… አታብጅ…” የሚል ሲሆን፣ በአዎንታ የቀረቡት ግን ሁለቱ ብቻ ናቸው። እነርሱም፥ “ሰንበትን አክብር… እናትና አባትህን አክብር…” የሚሉት ናቸው። እኔና እናንተ ቀና የሆነ አመለካከት ከሌለን፣ “አሥርቱ ትዕዛዛት አብዛኛዎቹ በአሉታ የቀረቡት እግዚአብሔር በፍቅር ሳይሆን በኃይልና በማስገደድ የሚገዛ አምላክ ነው” የማለት ዝንባሌ ሊኖረን ይችላል። “አድርግ… አታደርግ” የሚል ትዕዛዝ የሚያበዛ ጉልበተኛ አምላክ ነው” እንል ይሆናል። “ለአዲስ ኪዳን አማኞች ሕግ ምን ያደርጋል? ወቅታዊነት የሌለው ሕግና ሥርዓት ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ምን ድጋፍ ወይም አስተዋጽዖ ይሰጣል?” ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

## እግዚአብሔር የመምረጥና የመፍቀድን ነጻነት ሰጥቶናል

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው ሕግን ብቻ ሳይሆን፣ የመምረጥና የመፍቀድንም ሙሉ ነጻነት ሰጥቶታል። በምድረ ገነት ውስጥ የሚያስፈልገውን ሁሉ ከፈጠረለትና አመቻችቶ ካስቀመጠው በኋላ፣ ማድረግ ያለበትንና የሌለበትን ሕግ ሲነግረው፣ የመምረጥ ነጻነቱን በመግለጽ ይመስላል። እግዚአብሔር ለሰው የመፍቀድና የመምረጥ ነጻነት ባይሰጠው ኖሮ፣ ሰው የራሱ የሆነ ውሳኔ፣ የራሱ የሆነ ፈቃድ የሌለው፣ ካላስቀመጡት የማይቀመጥ፣ ካላንቀሳቀሱት የማይንቀሳቀስ ተራ አሻንጉሊት ብቻ ይሆን ነበር። የመምረጥና የመፍቀድ ነጻነት ባይኖረው ኖሮ፣ አንድ መልካም ያልሆነ ነገር ባደረገ ቁጥር፣ ያ ያደረገው ነገር በራሱ ፈቃድና ምርጫ ስላልሆነ፣ በኃላፊነት አያስጠየቀውም ነበር። የመጀመሪያው ሰው፣ አዳም የራሱ ፈቃድና ምርጫ ባይኖረው ኖሮ፣ “እንዳትበላ ያዘዝኩህን ነገር ለምን በላህ?” ብሎ እግዚአብሔር ሲጠይቀው፣ “እባቢቱ እንድበላ አደረገችኝ” በማለት የሰጠው መልስ ትክክል ይሆን ነበር። የራሱ ፈቃድ፣ የራሱ ምርጫ ስላለበት ነው አዳም ያቀረበውን ምክንያት እግዚአብሔር ያልተቀበለው። ሁሉንም የሚያውቀው ኃያሉ እግዚአብሔር፣ ሰው የራሱን ውሳኔ

መወሰን እንዲችል ሙሉ የመምረጥ ነጻነት ሰጥቶ ፈጠረው። ክፉውንና ደጉን የሚያሳየውን ፍሬ ካሳየው በኋላ፣ "መብላት' ወይም "አለመብላት" ምርጫው ያንተው የራስህ ነው" አለው። እግዚአብሔር ያወጀለት የመምረጥ ነጻነቱን ብቻ ሳይሆን፣ በሚመርጠው ምርጫ ተጠያቂ እንደሚሆንም ጨምር ነግሮታል።

ሰው የመምረጥ ነጻነት ባይኖረው ኖሮ፣ "ከዚህኛው ፍሬ አትብላ" የሚል ትዕዛዝ መስጠቱ ብቻ ይበቃ ነበር። "አትብላ.. ከበላህ ግን ትሞታለህ" ሲለው፣ የመምረጥ ነጻነት የሰጠው መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ስለዚህ አዳም ሁለት ምርጫ ነበረው። አንደኛው፣ "መብላት" ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ "አለመብላት" ነበር። ከቀረበለት ሁለት ምርጫዎች መካከል ደስ ያለውን ወይም የፈለገውን የመምረጥ ነጻነትና መብት ነበረው። ትክክለኛ የሆነውን ምርጫ፣ ይኸውም "የተከለከለውን ለመብላት" ቢመርጥ ግን፣ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍለው አስቀድሞ በማስጠንቀቂያ መልክ ተነግሮታል። አንዳንዶች እግዚአብሔር "አድርግ... አታድርግ... የሚል ትዕዛዝ ወይም ሕግ ለምን ይሰጣል? ሰው አንደልቡ መሆን እንዲችል ለምን ያለሕግ ወይም ያለትዕዛዝ ለምን አልተወውም?" በማለት ቅሬታቸውን ያሰማሉ። ያልተገነዘቡት ነገር ቢኖር ግን እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ እንጂ፣ የሥርዐተ አልባ አምላክ አለመሆኑን ነው። ሰው በሥርዓቱ እንዲኖር ድንበር አበጀለት። "በዚህ ክልል ውስጥ ካሉት ፍሬዎች የፈለግኸውን መብላት ትችላለህ፤ ከዚህ ውጪ ግን የተከለከለ ነውና አትብላ፤ ለአንተ የተሰጠ አይደለምና አትንካው" የሚል ገደብ ሰጠው። አሥርቱ ትእዛዛትን ሲሰጠው፣ ለምሳሌ "ከሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ደስ ይበልህ፤ የምታደርገው የሥጋ ግንኙነት ማድረግ የምትችለው ግን በጋብቻ ክልል ውስጥ ብቻ ነው" ማለቱ ነው። ይህንን የመሰለ ድንበር ማበጀቱ የፍቅር አምላክ መሆኑን ይቀንሰዋል ማለት አይደለም። ወላጆች የሆንን ልጆቻችን የፈለጉትን እንዲያደርጉ፣ የፈለጉበት ቦታ እንዲሄዱ ነጻነት አንሰጣቸውም። የምናወጣላቸው ገደቦች ወይም ድንበሮች አሉን። ካወጣንላቸው ድንበር ሲወጡ፣ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንሰጣቸዋለን። ገደብ የምናወጣላቸውና ከገደቡ ሲወጡ የምንቀጣቸው ስለምንወዳቸው እንጂ ስለምንጠላቸው አይደለም። ልንጠቅማቸው እንጂ ልንጎዳቸው አይደለም። ያለሕግ ወይም ያለገደብ ብንተዋቸው፣ ጉዳት ይደርስብናል ብለው ስለማያስቡ፣ በምንሰጣቸው ነጻነት ደስ ይላቸው ነበር። የምናወጣላቸው ገደብ ወይም ወሰን ደስታቸውን



ለመግፈፍ ሳይሆን፣ ከአደጋ ልንጠብቃቸው እንደሆነ በአዕምሯቸው ሲያድጉ ያውቁታል። እግዚአብሔርም ለሰው አሥርቱ ትዕዛዛትን ሲሰጥ፣ ሰውን ከጉዳት ለመጠበቅ እንጂ፣ ደስታውን ለመቀነስ እንዳልሆነ መረዳት ይገባናል። ስለዚህ አሥርቱ ትዕዛዛት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እንጂ፣ ጠላትነቱን አያሳየንም።

የመጀመሪያው ሰው፣ አዳም የመምረጥ ነጻነቱን ተጠቅሞ "መብላትን" ስለ መረጠ፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ ጣሰ። የምርጫው ውጤት ከፍተኛ ዋጋ አስከፈለው። ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን የተቀራረበ ግንኙነት ፈጽሞ አበላሸበት። ከሚወደውና ከሚያስብለት አምላኩ እንዲርቅ፣ እንዲሸሽ አደረገው። በመጨረሻም የሞትን ጽዋ እንዲቀምስ ምክንያት ሆነበት። በወቅቱ ራሱን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ እባብን ምክንያት አድርጎ ይጠቀምበት እንጂ፣ የችግሩ ዋና ምክንያት፣ እግዚአብሔር በሰጠው ሕግ ወይም መመሪያ ሥር ራሱን ማስገዛት ፈቃደኛ ስላልሆነ እንደሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ለሰው አሥርቱ ትዕዛዛትን በሲና ተራራ ላይ ሲሰጠው፣ በሕጎቹ እንዲፈላሰፍበት፣ ከአሰርቱ ትእዛዛት ውስጥ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የተለያዩ ሕጎችን እንዲያፈልቅበት ሳይሆን፣ ለመንገዱ ብርሃን እንዲሆንለት በማሰብ ነው። ሰዎች በዘመናት እነዚህን አሰርቱን ትዕዛዛት አውቀውታል፤ በቃላቸው አጥንተው በደንብ አንበለብለውታል። በቃላቸው ያንበለብሉት፣ እንደ ድግምት ይድገሙት፣ ይፈላሰፉበት፣ ብዙ ሕጎችን ይጨማምሩበት እንጂ፣ እግዚአብሔር በትእዛዛቱ ውስጥ የሚናገራቸውን ልብ ብለው ማስተዋል ግን አልሆነላቸውም። ስለ ሆንም፣ በትእዛዛቱ እንደሚገባው ሊጠቀሙበት አልቻሉም። ደህንነት ሲሆንላቸው ሲገባ፣ ወጥመድ ሆነባቸው። ሊመሩበት ሲገባ ሸክም ሆነባቸው። በተፈጥሮ ባላቸው የእምቢተኛነት ዝንባሌ፣ "አድርጉ" የተባሉትን ባለማድረግ፣ እንዲሁም "አታድርጉ" የተባሉትን በማድረግ በእግዚአብሔር ላይ አመጹበት። ከሁሉም የሚያሳዝነው እነዚህን የጌታ ትእዛዛት ወደ ሙሉነት ሊያደርሱን፣ ነጻነት ሊሰጡን፣ ከአደጋ ሊጠብቁን የሚችሉ የፍቅሩ መግለጫዎችና ማስጠንቀቂያዎች መሆናቸውን አውቀን በመቀበልና እንደ ትእዛዙ በመኖር ፈንታ፣ እንድንጎዳበት ብሎ ያመጣው እንደሆነ አድርገን የተቀበልነው መሆናችን ነው።

## ከእግዚአብሔር የተሰጠን መመሪያ ነው

አሥርቱ ትዕዛዛት ከእግዚአብሔር የተሰጡን ሕግና ደንቦች ናቸው። ማንም “እኔን አይመለከተኝም” ማለት የሚችል የለም። ሕይወታችንን እንዴት መምራት እንዳለብንና እንደሌለብን የሚያሳዩን መመሪያዎች ናቸው። ይሁን እንጂ ለብዙዎች አወዛጋቢ ወይም አከራካሪ ሆነዋል። እኔና እናንተ ባለንበት ሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን አንዳንድ ሕጎች ባንወዳቸውም፣ የግድ ሕግን አክብረን መኖር እንዳለብን እናውቃለን። ለምሳሌ ከምንፈልግበት ሥፍራ ቶሎ ለመድረስ መኪናችንን ከተወሰነው ፍጥነት በላይ ለማሽከርከር እንፈልጋለን። ፍጥነታችንን የሚገታ ነገር ቢኖር በምን ያህል ፍጥነት መኪናችንን ማሽከርከር እንዳለብን የሚገልጹ፣ በመንገዱ ዳር የቆሙ ምልክቶች ናቸው። እነዚህን ምልክቶች እንወዳቸውም። አንውደዳቸው እንጂ፣ ሕጉ በሚያዘው ፍጥነት መጠን መኪናችንን እንድ ናሽከረክር መመሪያ የሚሰጡን ምልክቶች ናቸው።

ተመልካች የለብንም በማለት ምልክቱን ችላ ብለን ከተወሰነው ፍጥነት በላይ ስንነዳ የትራፊክ ፖሊስ ቢያቆመን፣ የገንዘብ ቅጣት እንደሚደርስብን እናውቃለን። ጥፋተኛው የሚቀጣን የትራፊክ ፖሊሱ ሳይሆን፣ ከተወሰነው ፍጥነት በላይ በማሽከርከራችን ጥፋተኞቹ እኛው ራሳችን ነን። በገንዘብ መቀጣታችን ብቻ ሳይሆን፣ ደጋግመን ሕግ የምንጥስ ከሆን ደግሞ፣ መንጃ ፈቃዳችን ይወሰድብንና ለረጅም ጊዜ መኪና እንዳንነዳ እንታገዳለን። አንዳንዶቻችን ሕግ አክባሪዎች ባንሆንም፣ ቅጣቱን ስለምንፈራ ተጠንቅቀን እንነዳለን። ሕጉ ከሚያዘው ፍጥነት በላይ በመንዳታችን ቅጣቱ ሲደርስብን፣ ይህንዓይነቱን ሕግ ያወጡትን ሰዎችና እንዲሁም ሕግ አስፈጻሚ የሆነውን ትራፊክ ፖሊስ መጥላታችን አይቀርም። መረዳት የሚያቅተን ግን፣ ሕጉን ያወጡት ሰዎች ዓላማቸው እኛን ለመቅጣት፣ ወይም እኛን ለመጉዳት ብለው ሳይሆን፣ መኪናችንን በኃይል በመንዳት በራሳችንና በሌላው ሰው ሕይወት ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለመጠበቅ ነው። ይህንን እውነት ስንረዳ፣ እንወዳቸዋለን እንጂ አንጠላቸውም። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር አሥርቱ ትዕዛዛትን የሰጠን ሊጠቅመን ነው ወይስ ሊጎዳን? መልሱ ግልጽ ነው። ሊጠቅመን እንጂ ሊጎዳን አይደለም።



## መመሪያ ሕግ የተሰጠን እንዲጠቅመን ነው

አሥርቱ ትዕዛዛት ወይም ሕግ መጥፎ ነው፣ አይጠቅምም የሚሉ አንዳንድ ሰዎች የሚሰጡት የራሳቸው የሆነ ምክንያት አላቸው። “እንደልባችን መኖር እንዳንችል ሕግ ነጻነታችንን ያፍናል ወይም ይገፋል” ይላሉ። “አድርግ... አታድርግ...” የሚል ትዕዛዝ ስላለበት ነው አንዳንዶች “ክርስትና የፖሊስ ሃይማኖት ነው” የሚሉት። “ሕግን አክብረህ ከኖርክ ሁሉም ነገር በጎ ይሆንልሃል። አንዱን ሕግ እንኳን ጥሰህ ከተገኘህ ግን፣ የእግዚአብሔር ብርቱ ክንድ በአንተ ላይ ይሆናል” ይላሉ።

አንዲት ሚስዮናዊት አሥርቱ ትዕዛዛትን መሠረት በማድረግ አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ የቀበሌ መሪ የሆኑትን አፍሪካዊ፣ ክርስቲያን ለማድረግ ሙከራ አደረጉ። እኛ ሽማግሌ እኛ ሚስዮናዊት ሴት የሚነግሯቸውን ነገር በደንብ ከአዳመጡ በኋላ መጨረሻ ላይ “ምን ማለትዎ እንደሆነ በፍጹም አልገባኝም፤ የጎረቤትህን ሚስት መንጠቅ የለብህም ነው የሚሉኝ?” ብለው ጠየቁ። ሚስዮናዊቷም “አዎን!“ አሏቸው። “እንዲሁም በሬውንና ላሙንም መውሰድ የለብህም ነው ያሉኝ?” ብለው ጠየቋቸው። አሁንም “አዎን” የሚል መልስ ሰጧቸው። ቀጥለው “ጫካ ውስጥ ተደብቀህ የምትጠላውን ሰው መግደል የለብህም ነው ያሉኝ?” ብለው ጠየቋቸው። አሁንም “አዎን! በፍጹም” አሏቸው። እኛም ሽማግሌ በሀዘን ተሞልተው አንገታቸውን እየነቀነቁ፣ “አሁን ማድረግ የለብህም ያሉኝን ሁሉ እኔ በበኩሌ አላደርግም፤ የማላደርግበትም ምክንያት አቅም የሌለኝ ሽማግሌ በመሆኔ ነው። በዚህ ዓይነት ሽማግሌ መሆንና ክርስቲያን መሆን አንድ ዓይነት መሆኑ ይገርማል?” አሉ።

በዚህ ዓይነት ብዙዎች የክርስትና ሕይወትን ጊዜ ያለፈበት ወይም ከጊዜው ጋር የማይሄድ፣ ሁሉ ነገር ፍዝዝ ያለበት፣ ሰውን ፈጽሞ ደስታ የሸሸው የሚያደርግ እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል። እግዚአብሔር ለሰው አንድ ጊዜ ሕግ አውጥቶ ከሰጠ በኋላ፣ ሕጉን የማይጠብቁትን ሰዎች እየተከታተለ የሚቀጣ፣ ስለ ሰዎች ሕይወት ይህን ያህል ግድ የማይለው እንደሆነ አድርገው ይገምቱታል። ክርስቲያኖችን ወግ አጥባቂዎች፣ በሕግ የታሠሩ፣ በበአዊ ነጻነታቸውን ያጡ፣ በሃይማኖት ሠንሰለት የታሠሩ እንደሆኑ አድርገው የሚመለከቱ በአሁኑ ጊዜ ስንቶች ይሆኑ? ስለ እነርሱ የተሰጠውን ይህን ዓይነቱን ገለጻ ክርስቲያኖች በፍጹም ይቃወ

ራት የማይፈልግ አምላክ መሆኑን ያሳየናል። እውነተኛ እግዚአብሔር እርሱ ብቻ ስለሆነ፣ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ እንድናመልክ አይፈልግም። በኢሳያስ አማካኝነት ስለ ራሱ አምላክነት ሲናገር፣ "...እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም" ይላል (ኢሳ. 45፥18)።

➡ <u>ሁለተኛው ሕግ፥</u> "...በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ፤ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም" የሚለው ነው። እግዚአብሔር በሰው እጅ በተሠራ ምስል እንድናመልከው የማይፈልግ መሆኑን በግልጽ ይናገራል። እርሱ ሥጋዊ አካል ያለው ሳይሆን፣ መንፈስ ስለ ሆነ እንድንሰግድለት የሚፈልገው በመንፈስ እንደሆነ እንገነዘባለን።

➡ <u>ሦስተኛው ሕግ፥</u> "የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ አታንሳ" የሚለው ነው። ስሙን ያለአግባብ የሚያነሳው ሰው በደል አልባ አያደርገውም። እግዚአብሔር የተከበረ በመሆኑ ክብርን ይፈልጋል። ስሙ ቅዱስ ስለ ሆነ ያለአግባብ ስሙን የሚያቃልለውን ሁሉ የሚቀጣ መሆኑን ያሳያል።

➡ <u>አራተኛው ሕግ፥</u> "ሰንበትን አክብር" የሚለው ነው። ስድስት ቀን ሥርተህ በሰባተኛው ቀን እረፍ ይላል። ይሄም ሕግ እግዚአብሔር በየቀኑ ለሚሆነው ነገር ሁሉ እርሱ የበላይ መሆኑን ማሳየቱ ነው። እግዚአብሔር ራሱ በስድስት ቀን ውስጥ የመፍጠር ሥራውን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ ይናገራል። እኛም ሠርተን ስናርፍ፣ ሠርቶ ያረፈውን እግዚአብሔርን መታዘዛችን እንደሆነ እንድናውቅ ይፈልጋል።

➡ <u>አምስተኛው ሕግ፥</u> "እናትና አባትህን አክብር" የሚለው ሕግ ነው። ከዚህ ሕግ በስተኋላ የሚታየን ምን ይሆን? እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታችን በመሆኑ በእኛ ሕይወት ሙሉ ሥልጣን እንዳለው እናያለን። ከጥሩ ተስፋ ጋር የተያያዘ ትዕዛዝ፣ ይኼኛው ብቻ ነው። ይኸውም፣ "አባትህና እናትህን አክብር... ብታከብር ዕድሜህ ይረዝማል" ይላል።

➡ <u>ስድስተኛው ሕግ፥</u> "አትግደል" የሚለው ትዕዛዝ ነው። ለሰው ሕይወትን የሚሰጥ እርሱ ብቻ በመሆኑ፣ የሰጠውን መልሶ መውሰድ የሚያስችል ኃይልና ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ነው። ሌላው ቀርቶ ሰው ራሱም ቢሆን የራሱን ሕይወት ለማጥፋት መብትና ሥልጣን አልተሰጠውም። ይህን ሕግ ስናይ እግዚአብሔር ማንም ሥልጣኑን እንዲወስድበት የማይፈልግ አምላክ መሆኑን እንረዳለን።

➡ <u>ሰባተኛው ሕግ፥</u> "አታመንዝር" የሚለው ነው። ይሄስ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ የሚነግረን ምን ይሆን? እግዚአብሔር "ታማኝነትን የሚወድና የንጽህናና የቅድስና አምላክ" እንደሆነ ያሳየናል። በተጨማሪ የምንገባውን ቃል ኪዳን እንድንሰብር ሳይሆን እንድንጠብቅ የሚፈልግ መሆኑን እናያለን። በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ውስጥ የሚገኘውን ደስታ የሰጠ እርሱ በመሆኑ፣ ከጋብቻ ክልል ውጪ ይህንን ዓይነቱን ደስታ ለማግኘት መፈለጉን እንደሚጠላ እንገነዘባለን።

➡ <u>ስምንተኛው ሕግ፥</u> "አትሥረቅ" የሚለው ነው። ይህን ሕግ የሰጠን እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪና ሰጪ ስለሆነ፣ እርሱ ከሰጠን ውጪ ሌላ ነገር መፈለጋችንን የማይደግፍ መሆኑን ያሳየናል።

➡ <u>ዘጠነኛው ሕግ፥</u> "በሀሰት አትመስክር" የሚለው ሕግ ነው። በዚህም ሕግ ውስጥ እግዚአብሔር የእውነት አምላክ እንደሆነ እናያለን። ይሄ ትዕዛዝ የተሰጠው እውነተኛ ከሆነ እግዚአብሔር፣ የሚያደርገው ነገር ሁሉ እውነት ከሆነው አምላክ ነው። "የእስራኤል ክብር የሆነው እግዚአብሔር አይዋሽም" ይላል (1 ሳሙ. 15፥29)።

➡ <u>አሥረኛውና የመጨረሻው፥</u> "የባልንጀራህን ቤት አትመኝ" የሚለው ሕግ ነው። ምኞት እግዚአብሔር ከሰጠው ውጪ ሌላ ነገር እንዲኖረን የማይፈልግ መሆኑን ነው። ይህን ሕግ ስናፈርስ፣ የሚያስፈልገንን ሁሉ መስጠት በሚችለው ጌታ አለመተማመናችንን መግለጻችን ነው። እግዚአብሔር እንዳንመኝ የሚያዘን፣ የሚያስፈልገንን እርሱ እንደሚሰጠን አምነን በእርሱ መደገፍን በሕይወታችን እንድንለማመድ ስለሚፈልግ ነው። አሥርቱ ትዕዛዛትን ከላይ እንደገለጽነው የእግዚአብሔርን ባሕሪዎች ይኸውም ኃያልነቱን፣ ቀናተኛነቱን፣ ቅዱስነቱን፣ ክቡርነቱን፣ ታማኝነቱን፣ ሀቀኛ ወይም እውነተኛነቱን፣ ሰጪነቱንና እንዲሁም ፍቅር መሆኑን የሚገልጹ ናቸው።

ሰማይ ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን እነዚህን ትእዛዛት እየፈጸመ ሌሎችም እንዲፈጽሙ የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይባላል" ያለው (ማቴ. 5፡19)። የሙሴ ሕግ የእግዚአብሔር አብ ሕግ እንደሆነው ሁሉ የክርስቶስም ሕግ ነው። ትምህርታችን በጠቅላላው ትኩረት የሚሰጠው የሞራል ወይም የሥነ ምግባር ሕግ ላይ ነው። የሞራል ሕግ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚሠራ መሆኑን የምናረጋግጠው አሥሮችም ትዕዛዞች (ሕጎች) በአዲስ ኪዳን በአንድም ሆነ በሌላ፣ በክርስቶስ ወይም ሐዋርያት ባስተማሩት ትምህርት ውስጥ ተደጋግመው የተጠቀሱ መሆናቸውን ስናይ ነው።

የሰውን ሕይወት የሚያጎድፉ ኃጢአቶችንን ኢየሱስ ሲዘረዝር፣ በአሥርቱ ትዕዛዛት ላይ ያሉትን ሕጎች ይጠቅሳል። "ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ መግደል፤ ማመንዘር፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና ስም ማጉደፍ ከልብ ይመነጫልና። ሰውን የሚያረክሱ እነዚህ ናቸው..." ይላል (ማቴ. 15፡19)። እንዲሁም ሀብታሙ ሰው "የዘላለምን ሕይወት አገኝ ዘንድ ምን መልካም ነገር ልሥራ?" ሲል ለጠየቀው ጥያቄ ሲመልስለት፣ "...ወደ ሕይወት ለመግባት ከፈለግህ ግን ትእዛዛቱን ጠብቅ አለው። ሰውየውም የትኞቹን ትእዛዛት?' ሲል ጠየቀ። ኢየሱስም እንዲህ አለው 'አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፤ አባትህንና እናትህን አክብር፣ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ" አለው (ማቴ. 19፡16-17)።

<u>የመጀመሪያው ትዕዛዝ</u> "ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አይኑርህ" ይላል። ኢየሱስም ስለ ራሱ ሲናገር ይህን እውነት ያጸናል። "መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" አለ (ዮሐ. 14፡6)።

<u>ሁለተኛው ትዕዛዝ</u> "...በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ፤ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም" የሚለው ነው። ሐዋርያው ዮሐንስም "ልጆች ሆይ! ራሳችሁን ከጣዖት ጠብቁ" ይላል (1 ዮሐ. 5፡21)።

<u>ሦስተኛው ትዕዛዝ</u> የእግዚአብሔር ስምን እንድናከብር ያዛል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ስለ ጸሎት ሲያስተምራቸው በግልጽ ያቀረበው ይህንኑ ነው። "አባታችን ሆይ...ስም ይቀደስ..." ይላል (ማቴ. 6፡9)።

<u>አራተኛው ትዕዛዝ</u> ከሥራ ማረፍን የሚያዝ ነው። "ስለዚህ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ቀርቶለታል፤ ምክንያቱም ወደ



እግዚአብሔር ዕረፍት የሚገባ ሁሉ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፣ እርሱም ደግሞ ከሥራው ያርፋል" ይላል (ዕብ. 4፡9-10)።

የመጀመሪያዎቹ አራቱቹ እግዚአብሔርን ስለመውደድ የሚያዙ ናቸው። ጎረቤታችንንስ ስለ መውደድ የሚያዙት ትዕዛዞች የትኞቹ ናቸው?

<u>አምስተኛው ትዕዛዝ</u> "አባትህንና እናትህን አክብር" የሚለው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እየደጋገመ ስለዚሁ ትዕዛዝ በሚያስተምረው ትምህርት ይገልጻል። "ልጆች ሆይ! ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፤ ይህ ተገቢ ነውና። አባትህንና እናትህን አክብር በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ፤ መልካም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም የሚል ነው" ይላል (ኤፌ. 6፡1-3)።

<u>ስድስተኛ ትዕዛዝ</u> "አትግደል" የሚል ሲሆን፣ ኢየሱስ ደግሞ ይህኑ ትዕዛዝ ውድቅ በማድረግ ፈንታ ሲያጸናው "አትግደል የገደለ ይፈረድበታል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል..." ይላል (የማቴ. 5፡21)።

<u>ሰባተኛው ትዕዛዝ</u> "አታመንዝር" የሚል ሲሆን፣ ኢየሱስ ይህንንም ትዕዛዝ ሲያጸና፣ "አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል" ይላል (ማቴ. 5፡27-28)።

<u>ስምንተኛው ትዕዛዝ</u> "አትስረቅ" የሚለው ሲሆን፣ ጳውሎስ በትምህርቱ ይህንኑ ትዕዛዝ ሲመክር፣ "ይሰርቅ የነበረ ከእንግዲህ አይስረቅ፤ ነገር ግን ለተቸገሩት የሚያካፍለው ነገር እንዲኖረው በገዛ እጆቹ በጎ የሆነውን እየሠራ ለማግኘት ይድከም" ይላል (ኤፌ. 4፡28)።

<u>ዘጠነኛው ትዕዛዝ</u> "በሀሰት አትመስክር" የሚለው ሲሆን፣ አሁንም ይህንኑ ትዕዛዝ ጳውሎስ ሲያጸና፣ "...እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ" ይላል (ቆላ. 3፡9)።

<u>አሰረኛውና የመጨረሻው</u> መመኘትን የሚከለክል ሲሆን፣ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልዕክቱ ምዕራፍ 4 ቁጥር 3 ላይ "...ለራሳችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁ" በማለት የምኞትን ኃጢአት መሆኑን ይገልጻል።

ታዲያስ "አሥርቱ ትዕዛዛትን" በጸጋው ድነናል ብለን ችላ እንድንለው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል? ይህ እውነት እንዳልሆነ በግልጽ ከእግዚአብሔር ቃል ከላይ በሰፊው ተመልክተናል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን በምን ዓይነት ሁኔታ መኖር እንዳለብን ትክክለኛውን ያሳየናል። አሥርቱ ትዕዛዛት በእግዚአብሔር ቅድስና ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይህን እያወቅን አሥርቱ ትዕዛዛትን ችላ ልንል ይገባን ይሆን? ጳውሎስም "ከእምነት የተነሣ ሕግን ዋጋ የሌለው እናደርግ ይሆን? ፈጽሞ አይደረግም፤ ሕጉን እናጸናለን እንጂ" ይላል (ሮሜ 3፡31)። ይቀጥልና "...ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዙም ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው" ይላል (ሮሜ 7፡12)። አንድ ነገር ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር ግን፣ ሕግ መጠበቃችን ደህንነት የማያስገኝልን መሆኑ ነው። ሕግን በመጠበቅ መዳን የሚቻል ቢሆን ኖሮ ክርስቶስ መጥቶ የመስቀልን ሞት መቅመስ ባላስፈለገው ነበር። ሕግን በመጠበቅ የሚዳን ቢሆን ኖሮ ማንም ሰው ሕግን በሙሉ ለመጠበቅ ችሎታ ያለው ሰው ስለማይኖር፣ ሰው ሁሉ የጠፋና ለመዳን ተስፋ የሌለው ይሆን ነበር። ሕግን በሙሉ የጠበቀ ኢየሱስ ብቻ ነው። በእኛ ምትክ ሆኖ ሕጉን ሁሉ ጠበቀልን። ያ ብቻ ሳይሆን እኛ ሕግን ሁሉ መጠበቅ ባለመቻላችን ሊደርስብን የነበረውን ቅጣት እርሱ በጫንቃው ተሸክሞ ቅጣታችንን ወሰደልን። ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ይድናል። በክርስቶስ በማመን የምንድን ከሆንን ሕጎቹን ወይም ትዕዛዛቱን መጠበቅ ይኖርብናል? መልሱ "አዎን!" የሚል ነው። የሞራል ወይም የሥነ ምግባር ሕግ እግዚአብሔር በሕይወታችን በጽድቅና በቅድስና እንድንኖር እንደሚፈልግ የሚያሳይ በመሆኑ፣ አሥርቱን ትዕዛዛት እንድንጠብቅ ኢየሱስ ይመክረናል። የምንጠብቀውም ለመዳን ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ያስችለናል ብለን ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር ያስታረቀንን ጌታ ደስ ለማሰኘትና በቅድስና እንድንኖር ብቻ ነው።



# ምዕራፍ ሁለት

# በአግባቡ ከተጠቀምንበት "ሕግ" መልካም ነው

"ነገር ግን ሰው በአግባቡ ከተጠቀመበት
ሕግ መልካም መሆኑን እናውቃለን።"
(1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥8)

አሥርቱ ትዕዛዛት፥ በተለይ በምዕራቡ ዓለም፣ በአንዳንድ ግለሰብ ቤት፣ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ግድግዳ ላይ፣ በታላላቅ የሕዝብ ሕንጻ ላይ ተቀርጾ ይታያል። አሜሪካ ውስጥ በተለይ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ አሥርቱ ትዕዛዛት ከፍተኛ ክርክርና ግጭት የፈጠረ መሆኑ ይታወቃል። "አሥርቱ ትዕዛዛት በየትኛውም የመንግሥት ተቋም ውስጥ መቀመጥ የለበትም" በሚሉትና መገኘት አለበት በሚሉት መካከል ከፍተኛ ግጭት ተፈጥሮ የአገሪቱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት የቀረበ መሆኑ ይታወቃል። በተለይ በግልጽ የሚታወቁት በቴክሳስና በኬንታኪ እንዲሁም በአላባማ ስቴቶች ውስጥ የነበረው ክርክር ነው። በተለይ በ2003 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) የአላባማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩት የፌዴራሉ ፍርድ

ቤት ያዘዘውን ወይም የሰጠውን ውሳኔ፣ ይኸውም አሥርቱ ትእዛዛትን የያዘው ሀውልት (ቅርጽ) ከፍርድ ቤቱ ሕንጻ ይውጣ በማለት የሰጠውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ "አልቀበልም፤ አሥርቱ ትእዛዛትን የያዘውን ሀውልት አላነሳም" በማለታቸው ከያዙት ሥልጣንና ኃላፊነት የተባረሩ መሆናቸውን በዜና ማሰራጫዎች ሁሉ የተላለፈ ታሪክ በመሆኑ በብዙዎች ዘንድ የታወቀ ነው። ይህን ዓይነቱን ጭቅጭቅና ክርክር ስናይ፣ አንዳንድ ሰዎች ይህን ያህል ከፍተኛ ዋጋ የሚከፍሉት፣ ለእግዚአብሔር ሕግ ከፍተኛ ሥፍራ በመስጠት ይሆን? ወይስ ሌላ ምክንያት አላቸው። አንዳንዶቹ ለሚያደርጉት የፖለቲካ ትግል እንዲጠቀማቸው እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ ይገመታል። ይህን ያህል ከፍተኛ ዋጋ የሚከፍሉት ሰዎች፣ ለመሆኑ በግል ሕይወታቸው አሥርቱ ትዕዛዛትን ይጠቀሙበት ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የሚያስደንቀው፣ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ወግ አጥባቂዎች ወይም ሕግ አክራሪዎች እንኳ፣ ብዙዎች በግል ሕይወታቸው ሲለማመዱት ወይም ሲኖሩበት የሚታዩ አለመሆናቸው ነው።

ስለ ሕግ ብዙ የጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈለት በመጀመሪያው መልዕክቱ፣ *"ሕግን በአግባቡ ከተጠቀምንበት መልካም ነው"* ይለዋል (1 ጢሞ. 1፥8)። የእግዚአብሔር ቃል "ሕግ መልካም ነው" ካለ፣ በአሁኑ ዘመን ብዙዎች ችላ የሚሉት ምክንያቱ ምን ይሆን? ክርስቲያኖች፣ አሥርቱ ትዕዛዛትን ችላ የሚሉበት ምክንያት፣ በግል ሕይወታቸው እንዴት ሊጠቅማቸው እንደሚችል ባለማወቅ፣ እንዲሁም የወንጌሉን ቃል የማይቃረን እንደሆነ በቂ መረዳት የሌላቸው በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ሕጉን ለሰው ልጅ ሲሰጥ ሸክም እንዲሆንበት፣ ሃይማኖተኛ ሰው መሆኑን እንዲያሳይበት፣ ቤቱ ግድግዳ ላይ ጽፎ እንዲለጥፈው ሳይሆን፣ በራሱ ጥረት በቅድስና መኖር እንደማይችል እንዲያስገነዝቡት፣ በእግዚአብሔር ፊት ቅዱስ ሆኖ ለመገኘት እንዳይችል እንቅፋት ሊሆኑበት የሚችሉትን ኃጢአቶች ለይቶ እንዲያውቅበት ነው። አማኝ አሥርቱ ትዕዛዛት ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሕግ መሆኑን ቢያውቅም በትክክል ሊገለገልበት የሚችለው አጠቃቀሙን እንደሚገባው ያወቀበት እንደሆነ ብቻ ነው።



## ሕግ ያለው አገልግሎት

ሕግ ሦስት ዓይነት አገልግሎት እንዳለው የሥነ መለኮት ምሁራን ይገልጻሉ።

- አንደኛ፥ ደህንነትን ያገኙ አማኞች ለእግዚአብሔር ክብር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ይጠቁማል።
- ሁለተኛ፥ ሕግ ሕብረተሰቡ በአኗኗሩ ልቅ የሆነ ወይም ሥርዓት የለቀቀ ሕይወት እንዳይኖር ይገታዋል።
- ሦስተኛ፥ ኃጢአተኛው ሰው ሕግን በሙሉ በራሱ አቅም ሁሉንም መጠበቅ እንደማይችል ስለሚረዳ፣

ሕግን በመጣሱ ምክንያት ከሚደርስበት ዘላለማዊ ሞት እንዲያድነው፣ ፊቱን አዳኝ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ እንዲመልስ ያደርገዋል። ለመሆኑ ሕግ ለእግዚአብሔር ክብር እንዴት መኖር እንደምንችል የሚያስተምረን በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? ስለ አሥርቱ ትዕዛዛት የሚናገረው ክፍል፣ ዘፀአት ምዕራፍ 20 የሚጀምረው፣ በቀጥታ ትዕዛዛቱን በመዘርዘር ሳይሆን፣ *"እግዚአብሔር እነዚህን ቃሎች ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ ከግብጽ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ"* በማለት ነው (ዘፀ. 20፥1)። ይህን ካለ በኋላ ዐሥርቱ ትዕዛዛትን ተራ በተራ መዘርዘር ይጀምራል። ከላይ ባየነው ሁኔታ የተጻፈው ያለምክንያት እንዲሁ አይደለም። እነዚህ ትዕዛዛት ከታላቁና ከኃያሉ እግዚአብሔር የተሰጡ መሆናቸውን፣ ለሰው የሰጠውን ቃል ኪዳን ከሚያከብረው፣ እንዲሁም በተራራው ላይ ክብሩን በሚያስደንቅ ሁኔታ ከገለጸውና የማዳን ኃይል ካለው አምላክ የመጣ መሆኑን ለማሳየት ነው። ማንኛውም ዓይነት ትዕዛዝ ለከፍተኛነቱ ወሳኙ ትዕዛዙን የሰጠው ሰው በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ኃይልና ሥልጣን ነው። ከአንድ አገር መሪና እንዲሁም ከቀበሌ ማህበር ጸሀፊ የሚመጣውን ትዕዛዝ ሁለቱንም እኩል አናስተናግድም። ከአገር መሪ የሚመጣውን ትዕዛዝ የምንቀበለው በአክብሮትና በፍርሃት ነው። አሥርቱ ትዕዛዛትም ከሙሴ የመጣ ሳይሆን፣ ከራሱ ከኃያሉ እግዚአብሔር የመጣ ነው። ለዚህ ነው በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ተቀብለን ልንኖርበት የሚገባው።

ንና ልባችንን እናቀናለን። "መርፌ የተቀደደ ልብስ አይሰፋም፤ ነገር ግን ከክሩ በፊት እየቀደመ ክሩ የሚያልፍበትን ቀዳዳ ያበጃል" እንደሚባለው፣ ሕግም በራሱ ደህንነትን አይሰጥም፤ ይሁን እንጂ፣ ሰው በራሱ ጉልበት መዳን እንደማይችልና ወደ አዳኙ እንዲመለከት ያደርጋል። አንድ ጸሀፊ ሕግ ምን እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ አለ። "የእግዚአብሔር ሕግ እንደ መስታወት ነው። መስታወት ፊታችን መቆሸሹን ያሳየናል እንጂ፣ የቆሸሸውን ፊታችንን አያጸዳልንም። ፊታችንን በመስታወት ስናይ ቆሻሻ መኖሩን ቢያሳየን፣ ቆሻሻችንን ከፊታችን ላይ ለማስወገድ መስታወቱን አንስተን ፊታችንን አንጠርግበትም። መስታወቱ ቆሻሻችንን ያሳየን ውሃ ፈልገን እንድንታጠብ ነው።" ሕግም የሚጠቅመን በዚህ ዓይነት ነው። ደህንነት ሊሰጠን ሳይሆን፣ ልባችንን ሊያድነን ወደሚችለው ጌታ እንድናቀና የሚያሳስበን መሆኑ ነው።

እጅግ በጣም የሚያሳዝነው በዘመኗ ቤተ ክርስቲያን አሥርቱ ትዕዛዛት ወይም የእግዚአብሔር ሕግ ቦታ የሌለው መሆኑ ነው። እግዚአብሔር ያወጣው የቅድስና ደረጃ፣ ከወንጌል ጋር ያለውን ግንኙነት በአንዳንድ አብያት ክርስቲያናት በአሁኑ ዘመን እንደሚገባው የማይሰበክ መሆኑ ነው። እርግጥ ነው አሥርቱ ትዕዛዛት ሰዎችን አያዝናናም፤ ይቆረቁራል እንጂ አያመቻችም። እንዲያውም አንዳንዶችን ያስቆጣል። ይሁን እንጂ፣ የጠፉትን ለማዳን የግድ ይህ እውነት በየአብያተ ክርስቲያናቱ በኃይልና በሥልጣን መሰበክ አለበት። ኃጢአተኞች ኃጢአታቸው ሊሰማቸው የሚችለው የእግዚአብሔር ሕግ ወይም ትዕዛዝ ሲሰበክ ሲሰሙ ነው። አሥርቱ ትዕዛዛትን በአግባቡ መጠቀም የምንችለው፣ ሕጎቹን በትክክል ማየትና መተርጎም ስንችል ነው። ለዚህም የተለያየ መመሪያ አለን።

የመጀመሪያው መመሪያችን፣ እያንዳንዱን ሕግ ለመረዳት ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከርን ነው። አንድ ሥፍራ ብቻ የተጠቀሰውን ሀሳብ በመያዝ ሳይሆን፣ ጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚያ ሕግ ምን እንደሚል መመርመር አለብን። ለምሳሌ "...በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ። አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም..." የሚለውን ትዕዛዝ እንመልከት። ይሄ ትዕዛዝ በጣም ፊት ለፊትና ግልጽ በመሆኑ ሌላ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስልም። ይሁን እንጂ፣ ማምለክ ወይም ጣዖት የሚለውን አሳብ በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልገን ብናወጣ፣ ብዙ አሳብና መመሪያዎችን እናያለን። ኢሳያስ ሰዎች በእጃቸው የሠሩትን



ጣዖት እንዴት እንደሚያመልኩ በዝርዝር አቅርቧል (ኢሳ. 44:6-25)፣ እንዲሁም ኢየሱስ ለእግዚአብሔር እንዴት መስገድ እንዳለብን ሲገልጽ፣ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰገድለትም በመንፈስ ነው" ይላል (ዮሐ. 4:24)። ጳውሎስም ስስታምነት ጣዖትን እንደማምለክ እንደሆነ ይገልጻል (ኤፌ. 5:5)። አሥርቱ ትዕዛዛትን በደንብ ለመረዳት፣ ክርስቶስ እንዴት እንደተረጎመው መረዳት ያስፈልገናል።

ሕጎችን እንደሚገባው ለመረዳት የሚያስችለን ሁለተኛው መመሪያ የሰውን የውስጡንና የውጫዊ ሕይወቱን በመመልከት ነው። የእግዚአብሔር ሕግ ከውጪ ያለውን ሥጋዊ አካልን ብቻ ሳይሆን፣ ውስጣዊ ወይም መንፈሳዊ የሆነውንም ይመለከታል። ጳውሎስ "ሕጉ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለን" ይላል (ሮሜ 7:14)። ይህም ማለት የሚጠቅመው ለሥጋዊው ሕይወታችን ብቻ ሳይሆን፣ ለነፍሳችንም እንደሚያገለግል መግለጹ ነው። ሰው የሚሰጠው ሕግ ሥጋዊውን እንጂ መንፈሳዊ ሕይወትን አይነካም። እግዚአብሔር ውስጣዊ አቋማችንን፣ በተግባር ላይ ያዋልነው ብቻ ሳይሆን፣ ምን እንደምናስብም ያውቃል። "እግዚአብሔር የሚያየው ሰው እንደሚያየው አይደለም። ሰው የውጭውን ገጽታ ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" ይላል (1 ሳሙ. 16:7)።

ስለሆነም ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ የሚሆነው በሥጋው ለሚፈጽመው ኃጢአት ብቻ ሳይሆን፣ ማንም ሥጋ የለበሰ ሰው የማያየውን በልቡ፣ ወይም በሀሳብ ለሚፈጽመው ኃጢአት ጭምር ነው። አሥርቱ ትዕዛዛት መንፈሳዊነት እንዳለው በግልጽ መረዳት የምንችለው "...የባልንጀራህን ቤት አትመኝ..." የሚለውን አሥረኛ ትዕዛዝ ስናይ ነው። ይሄ ኃጢአት በተግባር ሲፈጽም የሚታይ አይደለም። አሥርቱ ትዕዛዛት መንፈሳዊነት ያላቸው ስለሆነ፣ የውስጣዊውንም ሆነ የውጪያዊውን ሕይወት ይነካል። ሰባተኛው ትዕዛዝ "አታመንዝር" የሚለው ሲሆን፣ ኢየሱስ ይህን ትዕዛዝ በስፋት እንድንመለከት ሲያደርገን፣ በተራራው ስብከቱ "አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር ያመነዘረ" ይላል (ማቴ 5:27-28)። ሰባተኛው ትዕዛዝ ከጋብቻ ውጪ የሆነውን ስጋዊ ግንኙነትን ብቻ ሳይሆን፣ የሥጋ ምኞትንም ይከለክላል።

ስለ አሥርቱ ትዕዛዛት አንዳንድ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው ሰዎች አሉ። አሥርቱ ትዕዛዛት ከጊዜው ጋር የማይሄዱና ፍጹም ያረጀ ነው

ይላሉ። ለዚህ አባባላቸው የሚሰጡት የራሳቸው ምክንያቶች አላቸው። በሰለጠነው ዓለም ሰዎች እንዲያደርጉ የታዘዙትን ሁሉ "ለምን?" የሚል ጥያቄ ሳያቀርቡ ዝም ብለው የተሰጣቸውን ትዕዛዝ የሚያደርጉ አይደሉም። ሕጻናት በአሁኑ ዘመን አስተማሪዎቻቸውና ወላጆቻቸውን "ለምን?" ብለው እንዲጠይቁ ያደፋፍሯቸዋል። አሥርቱ ትዕዛዛት እርግጥ ነው፣ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ ካላቸው አመለካከት ጋር አብሮ አይሄድም። "አታድርግ… አድርግ…" የሚል ትዕዛዝ እንጂ፣ በቅንፍ ለምን ማድረግ እንደሌለበት ወይም ማድረግ እንዳለበት ምክንያቱን አይዘረዝርም። *"ማንንም የማይጎዳ ከሆነ ከጋብቻ ክልል ውጪ የሩካቤ ሥጋ መፈጸም ስህተት የሚሆነው ለምንድነው? ልጆቹን የማያከብረውን፣ ጥዋትና ማታ እየገባ ልጆቹን የሚቀጠቅጠውን፣ መንፈሳቸውን የሚሰብረውን አባት ማክበር ለምን ያስፈልጋል? ስድስት ቀን ብቻ ለምን እንሠራለን? ሰባቱንም ቀን መሥራት ችግሩ ምንድነው?"* የሚል ጥያቄ ይጠይቃሉ። ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አሥርቱ ትዕዛዛትን ይዘረዝራል እንጂ፣ ከያንዳንዱ ትዕዛዝ በኋላ "ለምን?" ለሚለው ጥያቄ መልስ አይሰጥም።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈለት የመጀመሪያው መልዕክቱ *"…ሰው በአግባቡ ከተጠቀመበት ሕግ መልካም መሆኑን እናውቃለን" (1 ጢሞ. 1፥8)* እንዳለው ቀደም ሲል ተመልክተናል። ለመሆኑ ሕግ መልካም የሚሆንበት በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? ሕግ ነጻነታችንን ይጠብቃል። "ይጠብቃል" ስንል በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? ሕግ ለነጻነታችን ገደብን ያበጃል እንጂ፣ ነጻነታችንን እንዴት ይጠብቃል? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ስለ አሥርቱ ትዕዛዛት ትክክለኛ መረዳት ሲኖረን፣ ነጻ የሆነና ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንዲኖረን ያደርጋል። እውነተኛ መመሪያና ትክክለኛ የሆነ ምርጫ መምረጥን እንማርበታለን። በሕይወታችን ደስተኛ ለመሆን የምንመርጠው ምርጫ ወሳኝነት አለው። "እሺ!" ወይም "እምቢ!" የምንለው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን፣ እንዲሁም እርስ በርሳችን ለሚኖረን የተቀራረበ ግንኙነት ወሳኝ ነው። እግዚአብሔር የፈጠረን ለብቻችን ወይም በተናጠል እንድንኖር ሳይሆን፣ ከሰው ጋር በሚኖረን ግንኙነት ደስ ብሎን እንድንኖር ነው። አሥርቱ ትዕዛዛት በሙሴ ዘመን ለነበሩት ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ በአሁንም ዘመን ላለነው ሰዎች በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ይሄ ነው።



ደስታ፣ ሰላም፣ የሕይወት እርካታ ማግኘት የምንችለው በሕይወታችን የምንወስናቸው ውሳኔዎች "ፈሪሃ እግዚአብሔር ያልጎደላቸው" ሲሆኑ ነው። አሥርቱ ትዕዛዛት እግዚአብሔር ምን ዓይነት ባሕሪ እንዳለው፣ ምን ደስ እንደሚያሰኘው ወይም ምን እንደሚፈልግ ያመለክተናል። በሲና ተራራ እግዚአብሔር ግልጽ በሆነ ሁኔታ ተናገረ። እነዚህም ትዕዛዞች ግራ የሚያጋቡ፣ ተጨባጭነት የሌላቸው፣ አሳብ ብቻ ወይም ተራ ፍልስፍና የተደባለቀባቸው ሳይሆኑ፣ የሰውን የግል ሕይወት በቀጥታ የሚነኩ ናቸው። ሰው ለማየት ፈቃደኛ ከሆነ፣ ከትዕዛዙ ባሻገር የሕጉ ባለቤት ወይም ጌታ ትክክለኛ ማንነቱን በግልጽ ማየት ይችላል። ከእርሱም ጋር ሆነ፣ ሰው እርስ በርሱ የተቀራረበ ግንኙነት እንዲኖረውና በዚያም ደስ ብሎት እንዲኖር የሚፈልግ አምላክ መሆኑን ይገነዘባል። በአሥርቱ ትእዛዛት እግዚአብሔር የእርሱን ማንነት ብቻ ሳይሆን፣ የመምረጥ ሙሉ ነጻነትና ችሎታ የሰጠው መሆኑንም ያውቃል። ሰው የመምረጥ ችሎታና ሥልጣን ስለተሰጠው፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ "እሺ!" ወይም "እምቢ!" ማለት ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የመምረጥ ነጻነቱ ከኃላፊነት ወይም ከተጠያቂነት ነጻ እንደማያደርገው ማወቅ አለበት።

አሥርቱ ትዕዛዛት እንደ ሀሳብ ለሰው የቀረቡ አይደሉም። "ደስ ካለህ ታዘዛቸው፣ ደስ ካላለህ ግዴለም ተዋቸው" በማለት አልተሰጠውም። ቀጥተኛ የሆነ ትዕዛዝ ነው። ሕጎቹን የሚሰብራቸው ወይም የማይጠብቃቸው ከሆነ፣ አስፈላጊውን ቅጣት ያገኛል። እነዚህ ሕጎች ዓለም አቀፋዊ ናቸው። በዓለም ዙሪያ ከነዚህ ትዕዛዞች ነጻ የሆነ ወይም የማይመለከተው ሰው የለም። የምንኖረው ሕግ ጠብቆ ወይም ታዞ በሚኖር ሕብረተሰብ፣ እንዲሁም የተፈጥሮ ሕግ በሚሠራበት ዓለም ውስጥ ነው። የተፈጥሮን ሕግ ችላ ብንል፣ ለምሳሌ የቤታችን ጣራ ላይ ወጥተን ጫፉ ላይ ለመቆም ብንሞክር፣ ግራቪቲ ወይም ስበት ወደ ታች ስቦን ስለምንወድቅ መጎዳታችን እንደማይቀር ግልጽ ነው። ልክ እንደተፈጥሮ ሕግ፣ የሞራል ወይም የመንፈሳዊ ሕግ አለ። እነዚህን ሕጎች ብንሠብር የሚደርስብን ሥጋዊና መንፈሳዊ አደጋ ይኖራል። መጽሐፍ ቅዱስ "ኃጢአት እየሠራች የምትኖር ነፍስ ትሞታለች" ይላል። ኃያሉ እግዚአብሔር ሞራላችንና መንፈሳዊ ሕይወታችንን በትክክል መምራት እንድንችል፣ ፍቅርና ነጻነትን እንዲሁም ዓላማና ትርጉም ያለበትን ሕይወት የምናገኝበት መመሪያ እንዲሆነን አሥርቱ ትዕዛዛትን ሰጥቶናል።

# አሥርቱ ትዕዛዛትን ማወቅ ወግ አጥባቂ ያደርገን ይሆን?

አንዳንድ ክርስቲያኖች "በአሥርቱ ትዕዛዛት ላይ ትኩረት መስጠት፣ ሕግ አጥባቂ ወይም ሕግ አክራሪ መሆን ነው" ይላሉ። "ግልጽ የሆኑትን፣ የምናውቃቸውን አሥርቱ ትዕዛዛትን እንኳን መጠበቅ እንደማንችል እያወቅን፣ ጠለቅ ብሎ መመርመሩ ይህን ያህል ምን ያስፈልጋል? የበለጠ ወግ አጥባቂዎች ወይም ሕግ አክራሪዎች አያደርገንም ወይ? ብለው የሚጠይቁ አሉ። በመሠረቱ የበለጠ ሕግ-አጥባቂዎች የምንሆነው ሕጉን እንደሚገባው ማወቃችን ሳይሆን አለማወቃችን እንደሆነ የተገነዘቡት አይመስሉም። ለምሳሌ እግዚአብሔር "አትግደል" የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶናል በማለት ሌላውን አለመግደላችን፣ ሕጉን የጠበቅን መስሎ ሊሰማን ይችላል። ነገር ግን ይህን "አትግደል" የሚለውን ስድስተኛውን ትዕዛዝ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉትን ሁሉ በጥንቃቄ ብንመረምር፣ "መግደል" የሚለው ቃል ሌላውን መጥላት፣ በሌላው ላይ ቁጣን ያለአግባብ መግለጽን የሚያጠቃልል መሆኑን እንገነዘባለን። ኢየሱስ "ለቀደሙት ሰዎች 'አትግደል' የገደለ ይፈረድበታል' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን ጅል የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል፤ ደደብ የሚለው ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል" አላቸው (ማቴ. 5፡21-22)። እንዲሁም "አታመንዝር" የሚለውን ትእዛዝ፣ "የሙሴ ሕግ እናንተን አይመለከታችሁምና አታስቡ" በማለት ፈንታ፣ ኢየሱስ ሲያጸናውና በስፋት እንድንመለከተው ሲያደርገን እናያለን። "አታመንዝር' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል" (የማቴ. 5፡27) ይላል። ታዲያ ይህን ማለት ሕግ አክራሪነት ወይም አጥባቂነት ነው? ፈጽሞ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ ቅድስና የሰጠውን ከፍተኛ ሥፍራ ወይም ደረጃ ዝቅ አድርገን እንዳንመለከት ይረዳናል። ቅድስና ምንን እንደሚያጠቃልል ስንረዳ፣ ቅድስናን ዝቅ አድርገን እንዳናይ ወይም ያለውን ከፍተኛ ድረጃ አሳንሰን እንዳንመለከት ይረዳናል።

ወግ አጥባቂነት ወይም "ሕግ አክራሪነት" ስንል ምን ማለታችን ይሆን? ሕግ አክራሪነት ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ የሆኑ ሕግና ሥርዓቶችን መጠ



በቅ ነው። ጳውሎስ የገላትያ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን ስለ ደህንነት ካስተማራቸው ትምህርት ውጪ ሌሎች ከአይሁድ እምነት የመጡ "ለመዳን የሙሴን ሕግ መጠበቅ፣ መገረዝ ያስፈልጋችኋል" ይሏቸው ነበር። ይኼ ክርስቶስ ካስተማረው መሠረታዊ ከሆነ ትምህርት ውጪ፣ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚችሉት በእምነት ብቻ ነው የሚለውን የሚቃረን ነበር። ለዚህ ነው ጳውሎስ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል ስለተባለ፣ ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይጸድቅ ግልጽ ነው። ሕግ በእምነት ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ ነገር ግን ሕግጋትን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ በሕይወት ይኖራል ተብሏል" (ገላት. 3፡11-12) ያለው።

የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ወይም ሕግጋት የተለያየ አገልግሎት ወይም ጥቅም ስላለው፣ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ማወቅ እንደሚገባን ደጋግመን ገልጸናል። አሥርቱ ትዕዛዛት ከሚሰጠው አገልግሎት አንደኛው፣ ኃጢአታችንን እንዲሁም አዳኝ እንደሚያስፈልገን እንድናውቅ ማድረግ ነው። ስለዚህ ሕግ ወደ ኢየሱስ እንድንመለከት ያደርገናል። ጳውሎስ ሮሜ 10፡4 ላይ፣ "ለሚያምን ሁሉ ጽድቅ ይሆን ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና" ይላል። ይህን ሲል፣ የሕግ ዋና ዓላማ ኢየሱስን ያመለክታል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ሕግ ምንን እንደሚጠይቅ በደንብ መረዳት፣ የእግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያዘጋጀልንን ጸጋ የበለጠ በግልጽ እንድንረዳ ያስችለናል። በአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ የተዘረዘሩት፣ የሥነ ምግባር (የሞራል) ሕጎች፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ትክክለኛ ማንነትና እንዲሁም ሥራውን የሚገልጹት በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን?

አንደኛው፣ ለእግዚአብሔር አብ የነበረውን የክርስቶስን ፍጹም ታዛዥነት ያሳየናል። መጽሐፍ ቅዱስ "ነገር ግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፣ ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ ይህም የሆነው የልጅነትን መብት እናገኝ ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ለመዋጀት ነው" ይላል (ገላት. 4፡4-5)። የእግዚአብሔር ሕግ የሰውን ውስጣዊ ሕይወት ይመረምራል። ለቅድስና የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በውስጡ ይዟል። ከእነርሱ ውስጥ ሥጋ የለበሰ ሰው አንዱንም እንኳን መጠበቅ አይችልም። ጴጥሮስ በ1ኛ መልዕክቱ 2፡22 ላይ ስለ ኢየሱስ ሲናገር፣ "እርሱ ኃጢአትን አላደረገም፤ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም" ይላል። ይህን ሲል፣ በእኛ ምትክ ሆኖ እያንዳንዱን ሕግ መፈጸሙን ሲገልጽ ነው። በእምነት ከእርሱ ጋር ከተያያዝን፣ እግዚአብሔር የሚያየን

## ምዕራፍ ሦስት

# ሕይወት የሌላቸው አማልክት አይኑርህ

"ከእኔ በቀር ለሌሎች አማልክት አይኑርህ።"

(ዘፀአት 20፥3)

*በምዕራቡ ዓለም ወላጆች ልጆቻቸው ገና ከህጻንነት ዕድሜያቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ከሚፈልጓቸው የተለያዩ መልካም ከሆኑ ባህሪዎች ማካከል አንደኛው፣ ያላቸውን መልካም ነገር ለሌሎች ሰዎች ማካፈልን ነው። ለምሳሌ፣ ከረሜላ ወይም ጣፋጭ ብስኩት ቢይዙ፣ ከጓደኞቻቸው ወይም ከወንድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው ጋር ተካፍለው እንዲበሉ፣ እንዲሁም ባላቸው መጫወቻ አብረው እንዲጫወቱ ይመክሯቸዋል። በዚህ ዓይነት የሚያድጉ ልጆች ብዙ ጊዜ ሙሉ ሰው ሲሆኑ፣ ያላቸውን መልካም ነገር ለሌሎች ማካፈል፣ ወይም ተካፍሎ መብላት ከባድ አይሆንባቸውም። ይሁን እንጂ፣ ሰው ምንም ያህል ለጋስ ቢሆኑ፣ ለማንም ማካፈል የማይፈልገው አንዳንድ ግላዊ የሆኑ ነገሮች እንዳሉት የታወቀ ነው።*



*ለምሳሌ የኑሮ ጓደኛውን ፍቅር፣ ምንም ያህል ለጋስ ቢሆን፣ ምንም ያህል ቢወደው ለሌላ ሰው ማካፈል ወይም ማጋራት ፈቃደኛ የሚሆን ሰው ይኖራል ብለን መገመት ያስቸግረናል። ሰው የሚወዳትን የኑሮ ጓደኛውን ፍቅር ማንም እንዲካፈልበት እንደማይፈልገው ሁሉ፣ በስጦታው በጣም ቸርና ለጋስ የሆነው እግዚአብሔርም፣ ስለ ደህንነታቸው ሲል አንድ ልጁን መስዋዕት አድርጎ የሰጠላቸውን፣ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚወዳቸው ልጆቹ ፍቅራቸውን፣ እንዲሁም ታማኝነታቸውን ከእርሱ በቀር ለሌሎች አማልክት እንዲሰጡ ወይም እንዲያጋሩ ፈጽሞ አይፈልግም። ወሰን በሌለው ምሕረትና ፍቅር የተሞላ፣ እንዲሁም ቸርነቱና ጸጋው የተትረፈረፈ አምላክ ቢሆንም፣ አምላክነቱንና ክብሩን ግን ማንም እንዲካፈልበት ወይም እንዲጋራበት አይፈቅድም። እግዚአብሔር ክብሩንም ሆነ አምላክነቱን ሰውም ሆነ አማልክት እንዲጋሩት ስለማይፈልግ ነው፣ ለሰው "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑርህ" የሚል የመጀመሪያውን ትዕዛዝ የሰጠው።*

*በታላቅነቱ እርሱን የሚመስል፣ በኃይልም ሆነ በሥልጣን የሚወዳደረው፣ ወይም ከእርሱ ጋር ተቀራራቢነት ያለው፣ ወይም "ከእግዚአብሔር ቀጥሎ" ወይም "በሁለተኛ ደረጃ ነው" የሚባል ሌላ አምላክም ሆነ ኃይል የለም። አምልኮታችንን ብቻ ሳይሆን፣ በጠቅላላው "የእኛ ነው" የምንለው ነገር ሁሉ ከእርሱ የተቀበልነው በመሆኑ፣ እኛነታችንንም ሆነ "የእኛ ነው" የምንለውን ሁሉ ለማንም ሳናካፍልና ምንም ሳናስቀር ሙሉ በሙሉ ለእርሱ እንድንሰጠው ይፈልጋል። ከሰማይ በላይም ሆነ ከሰማይ በታች አሉ ለሚባሉት ሌሎች አማልክት ለእርሱ ብቻ የሚገባውን ክብር ግማሹን ከፍለን፣ "ይሄ የአንተ ድርሻ ነው" ብለን እንድንሰጠው አይፈቅድም። ያለንን ቁሳቁሳዊ የሆነውን ነገር ብቻ ሳይሆን ሁለንተናችንንም፣ ለማንም ሳናጋራ ያለንን ሁሉ ለእርሱ እንድንሰጠው ይፈልጋል። አሥርቱ ትዕዛዛት ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ብቻ የተገባ እንደሆን በማወጅ ይጀምራል።*

*ከማንኛውም ነገር የበለጠ እግዚአብሔር በሕይወታችን የመጀመሪያውንና ከፍተኛውን ሥፍራ መያዝ እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ሥፍራ በግልጽ ይናገራል። አስቀድመን "የእግዚአብሔርን መንግሥት" የምንሻ ከሆነ፣ የጌቶች ጌታ፣ የንጉሦች "ንጉሡ" የሆነው ኃያሉ እግዚአብሔር በሕይወታችን የመጀመሪያውን ሥፍራ ወይም ደረጃ እንዲይዝ መፍቀድ አለብን። ለዚህ ነው "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑርህ" የሚለውን የመጀመሪያውን ትዕዛዝ የሰጠን። እግዚአብሔር አሥርቱ*

ትዕዛዛትን በሰጠበት ወቅት፣ እስራኤላውያን ወደ ባዕድ አምልኮት የመሳብ ዝንባሌ በነበራቸው ጊዜ ስለ ነበር፣ የመጀመሪያው ትዕዛዝ ከባዕድ አምልኮታቸው እንዲገቱ ለማሳሰብ የተሰጣቸው ትዕዛዝ እንደነበረ ግልጽ ነው። እስራኤላውያን በግብጽ ባርነት ውስጥ በነበሩበት ዘመን ለብዙ ዓመታት ብዙ እውነትነት የሌላቸው አማልክት ሲመለኩ ያዩና የተለማመዱ ሕዝቦች ነበሩ። ግብጻውያን በአንድ አምላክ ብቻ ሳይሆን በብዙ አማልክት ወይም ጣዖታት የሚያምኑ ሕዝቦች ነበሩ። ወንዙን፣ ተራራውን፣ ሸለቆውን፣ ጸሀይና ጨረቃን እንዲሁም ከዋክብትን እንደ አምላክ አድርገው በመቁጠር ይሰግዱላቸው ነበር። እስራኤላውያንም ብዙ አማልክት በሚመለክበት ሕብረተሰብ ውስጥ ለረጅም ዘመናት በመኖራቸው፣ የግብጻውያን ባሕልና ልምምድ በእነርሱ እምነት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አድርጎባቸው ነበር። ግብጻውያን፣ አምላክ ብለው የሚሰግዱላቸውን ጣዖታት ሁሉ እስራኤላውያንም ይሰግዱላቸውና ያመልኳቸው ነበር።

እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት ነጻ ሆነው ቢወጡም፣ ቀደም ሲል ወደተለማመዱት ወደ ጣዖት አምልኮት የመሳብ ዝንባሌ ነበራቸው። ይህ በመሆኑ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በየጊዜው ሌሎች አማልክትን በማምለክ ያሳዝኑት ነበር። ይህንኑ በነብዩ በሕዝቄል አማካኝነት ሲገልጽ፣ *"እነርሱ ግን በእኔ አመጹ፤ ሊሰሙኝም አልፈለጉም፤ ዐይኖቻቸውን ያሳረፉባቸውን ርኩስ ምስሎች አላስወገዱም"* (ሕዝ. 20፥8-9) ይላል። ይሄ የመጀመሪያው ትዕዛዝ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ዘመን ላለነው አማኞችም በጣም አስፈላጊ ነው። ብዙዎቻችን በአፋችን *"እግዚአብሔርን እወዳለሁ፤ በሕይወቴ ቅድሚያን የምሰጠው ለእርሱ ነው"* እንበል እንጂ በሕይወታችን ከፍተኛውን ሥፍራ የሰጠናቸው፣ ጣዖት የሆኑብን ቁሳቁሳዊ ነገሮችና እንዲሁም ሰዎች አሉን። እነዚያ ከእግዚአብሔር የበለጠ የምንወዳቸው፣ በሕይወታችን ከፍተኛውን ሥፍራ የሰጠናቸው ሰዎች ጣዖት ሊሆኑብን እንደሚችሉ የታወቀ ነው።

## ጣዖታችን ምንድነው?

ለመሆኑ የእኔና የእናንተ አምላክ ወይም እግዚአብሔር ማን ይሆን? ከእግዚአብሔር የበለጠ የምንወዳቸው ማንኛቸውም ነገሮች ወይም ሰዎች ጣዖት ሊሆኑብን እንደሚችሉ ተገንዝበን ይሆን? ምንጊዜም ቢሆን እግዚአ



ብሔር አንደኛ እንጂ፣ ሁለተኛ መሆን አይፈልግም። እርሱ ፍጹም የሆነ ኃያል አምላክ፣ የንጉሦች ሁሉ ንጉሥ፣ የጌቶች ሁሉ ጌታ ስለሆነ፣ በሁለተኛ ደረጃ መታየት አይፈቅድም። *"ከግብጽ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ..ከእኔ በቀር ሊሎች አማልክት አይኑርህ"* ሲል፣ ክብሩን ለማንም ማካፈል ወይም ማጋራት እንደማይፈቅድ መግለጹ ነው። በጅምላ ሳይሆን በተናጥል ለእያንዳንዱ እስራኤላውያን በነፍስ ወከፍ እንደተናገረ የምንረዳው፣ *"ከግብጽ ከባርነት ምድር ያወጣኋችሁ..."* በማለት ፈንታ፥ *"ከግብጽ ምድር ያወጣሁህ..."* በማለት መናገሩ ነው። በዘመኑ ያለነውም ሰዎች፣ አሥርቱ ትዕዛዛት በተሰጠበት ዘመን የነበሩትን ሰዎች የምንመስልበት ነገር አለን። በአሁኑ ጊዜ ያሉን ጣዖታትም አንዳንዶቹ ከጥንቶቹ ጣዖታት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው። በአሁኑ ዘመን ላለነውም ሰዎች እግዚአብሔር ሊያስተላልፍልን የሚፈልገው መልዕክት፣ *"ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ ስለሌለ፣ ...በአሳብህ፣ በሕይወትህ፣ በኑሮህ... እንዲሁም በዕለታዊ ሥራህ እኔን ብቻ አስቀድም"* የሚል መልዕክት ነው።

*"እስራኤላውያን፣ ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣቸውን፣ ትልቅ ውለታ የዋለላቸውን እግዚአብሔርን ትተው ሌሎች አማልክትን ወደማምለክ እንዴት አዘነበሉ?"* ብለን በመደነቅ መጠየቃችን አይቀርም። በችግራቸውና በጭንቀታቸው ወቅት የደረሰላቸውን አምላክ ከተስፋይቱ ምድር ሲገቡ፣ ሁኔታዎች ጥሩ ሲሆንላቸው ፈጥነው የሚረሱት መሆኑን የሚያውቀው አምላክ፣ *"አምላክህ እግዚአብሔር ለአንተ ለመስጠት ለአባቶችህ ለአብርሃም፣ ለይስሃቅና ለያዕቆብ ወደ ማለላቸው ምድር ሲያስገባህ፣ በዚያም ያልሠራሃቸውን ታላላቅና ያማሩ ከተሞችን፣ የራስህ ባልነበሩ መልካም ነገሮች ሁሉ የተሞሉ ቤቶችን ያልቆፈርሃቸውን የውሃ ጉድጓዶች፣ ያልተከልሃቸውን የወይን ተክሎችን የወይራ ዛፎች ሲሰጥህና በልተህም ስትጠግብ፣ ከባርነት ምድር ከግብጽ ያወጣሁህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ"* በማለት አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸው ነበር (ዘዳ. 6፥10-12)። ይህንን የመሰለ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም እስራኤላውያን እየደጋገሙ ልባቸውን ወደ ጣዖት አምልኮት በመመለስ በጎ ያደረገላቸውን አምላክ ያስቀይሙትና ያሳዝኑት እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ችግራቸው ለመሆኑ ምን ነበር? የእነርሱ ችግር በአሁኑ ጊዜ ካለነው ሰዎች ችግር ጋር ተመሳሳይነት ይኖረው ይሆን?

እኔና እናንተስ በሕይወታችን እግዚአብሔርን ማስቀደም አስቸጋሪ የሚሆንብን ምክንያት ምን ይሆን? እግዚአብሔርን ማስቀደም ከባድ የሚሆነው ለእኛ ብቻ ሳይሆን፣ በእምነታቸው "ብርቱ ናቸው" ለሚባሉትም፣ ከእኛ ቀድመው መጥተው ላለፉትም ሰዎች ጭምር ነው። አንድ ጊዜ፣ የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆኑ አንድ አሜሪካዊ፣ "የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ከሚያጋጥሙት ችግሮች ውስጥ ከባዱ የትኛው ነው? እርሶ በረጅሙ የአገልግሎት ዘመንዎ ውስጥ ከባድ ሆኖ ያገኙት የትኛው ኃላፊነት ነው? መስበክ ነው? ችግር ላለባቸው ምዕመናን የምክር አገልግሎት መስጠት ነው? ወይስ ማስተዳደር?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፣ "በአገልግሎቴ ውስጥ በጣም ከባድ ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ያገኘሁት፣ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አይደሉም። እውነት ነው፣ እነዚህ ሁሉ ከፍተኛ ጉልበትና ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው። ቢሆንም፣ ከነዚህ ሁሉ የበለጠ ሌላ አስቸጋሪ ነገር አለ። በየዕሁዱ በማቀርበው መልዕክት የብዙ ሰዎችን ሕይወት የሚነካ ወይም የሚለውጥ ትምህርት ባቀርብ፣ በሥነ ምክር አገልግሎት የብዙዎችን ትዳር ከመፍረስ ባድን፣ በቤተ ክርስቲያናችን ያሉትን ተባባሪ አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያኒቱን ትልቅ በጀት የማስተዳደር ብቃት ኖሮኝ በመልካም ሁኔታ ባስተዳድር፣ በጌታ ዓይን ሲታይ ግን፣ ፍጹም ፍሬ ቢስ ወይም ዋጋ የሌለኝ ልሆን እችላለሁ። በሕይወቴ በየቀኑ ማድረግ የሚያቅተኝ አንድ ነገር ቢኖር፣ ከጌታዬ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ይዤ መኖር፣ በሕይወቴ እርሱን ከሁሉ ነገር በላይ ማስቀደም፣ ከእርሱ ጋር በቂ ጊዜ ማሳለፍ ነው" አሉ። ይሄ የእርሳቸው ብቻ ሳይሆን፣ የብዙዎቻችንም ችግር ነው። ከእግዚአብሔር በፊት የምናስቀድመው፣ ጊዜያችንና ጉልበታችንን የምንሰጠው ምድራዊም ሆነ መንፈሳዊ ነገር፣ ሌላው ቀርቶ አገልግሎታችንም እንኳን ቢሆን፣ ከእርሱ ጋር በቂ ጊዜ እንዳናሳልፍ የሚያደርገን ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ቅር ያሰኘዋል እንጂ አያስደስተውም።

በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አማኞች ተስፋቸው የማይጠፋ ወይም ዘላቂነት ያለው እንዲሆን፣ እምነታቸው ጤናማ ሆኖ እንዲዘልቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ እንደ ነበር የራዕይ መጽሐፍ ይገልጻል። ይሁን እንጂ፣ "...የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ይኸውም የቀድሞውን ፍቅርህን ትተሃል" በማለት የነበረባቸውን ድካም ይገልጻል (ራዕ. 2፡4)። በዕለታዊ ሥራችን የሚያስመሰግነን ሥራ መሥራታችን፣ ጥሩ መንፈሳዊ ትምህርት ተምረን ረቂቅ የሆነ ምስጢር መግለጻችን፣ እንዲሁም በአገልግ



ሎታችን ብርቱ ሆነን መቆም መቻላችን ብቻ በቂ አይደለም። ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገታችን፣ እንዲሁም ጌታን ደስ ለማሰኘት ከእርሱ ጋር የሚኖረን የተቀራረበ ግንኙነት ወሳኝነት ስላለው፣ በልባችን ውስጥ ለእርሱ የምንሰጠው ሥፍራ ወይም ደረጃ የመጀመሪያው መሆን እንዳለበት ማወቅ ይገባናል። ንጉሥ ሠለሞን "በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤ እርሱም ጎዳናህን ቀና ያደርገዋል" ይላል (ምሳሌ 3፡5-6)። ሠሎሞን ይህን ቃል የተናገረው፣ የመጀመሪያውን ትዕዛዝ ከሕጻንነት ዕድሜው ጀምሮ ቢያውቅም፣ በግል ሕይወቱ ግን ያልተለማመደው በመሆኑ፣ በእርሱ ሕይወት የደረሰበትን ጉዳት ተገንዝቦ ሌሎችን ለማስጠንቀቅ የተናገረው ወይም የጻፈው ይሆናል ብለን እንገምታለን።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን "ከግብጽ ከባርነት ምድር ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ.." ሲላቸው፣ ያደረገላቸውን ውለታ አስታውሰው ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ እንዳያመልኩ ለማስጠንቀቅ ነው። አንድ ሰው በጎ ነገር ቢያደርጉልን፣ ውለታውን የምንመልስበትን መልካም ነገር በልባችን ማሰባችን አይቀርም። እግዚአብሔርስ ስላደረገልን በጎ ነገር ውለታውን ለመመለስ በልባችን የሚመላለስ ነገር ይኖር ይሆን? አንድ ጊዜ አንድ የስምንት ዓመት ልጅ ከክፍሉ ተማሪዎች ጋር ፈተና ይወስድ ነበር። ለፈተናው እንደሚገባው የተዘጋጀ ባለመሆኑ የተሰጠውን ፈተና በጊዜ መጨረሱን ስለተጠራጠረ በፍርሃትና በጭንቀት ተሞልቶ ይንቀጠቀጥ ነበር። በጣም ከመስጋቱ የተነሳ ሳያውቀው ሽንቱን ሱሪው ላይ ለቀቀው። በድንጋጤና በፍርሃት ተሞልቶ ጎንበስ ብሎ መሬት መሬት ሲመለከት፣ ሽንቱ ወለሉ ላይ ተንጣሎ አየ። የበለጠ ደነገጠ። በጭንቀትና በድንጋጤ ተሞልቶ ቀና ብሎ ሲመለከት፣ አስተማሪው በፊቱ ገጽታ ላይ ድንጋጤና ፍርሃት ስላየች፣ ጥያቄ ካለው እንዲጠይቃት ወደ እርሷ እንዲመጣ ምልክት አሳየችው። ይሁን እንጂ፣ ከተቀመጠበት መንቀሳቀስ አልቻለም። ምክንያቱን ባታውቅም መንቀሳቀስ አለመቻሉን የተረዳችው አስተማሪው ከመቀመጫዋ ተነስታ ወደ እርሱ ስትመጣ ሲያይ፣ "ወይኔ! እንግዲህ ምን ማድረግ እችላለሁ? ወለሉ ላይ የተንጣለለውን ሽንቴን ልታይብኝ ነው። የተማሪዎች ሁሉ መሳቂያና መቀለጃ መሆኔ ነው! ምን ዓይነት አሳፋሪና ክፉ ነገር ደረሰብኝ" እያለ በዚያች አጭር ጊዜ ከራሱ ጋር ይነጋገር ነበር።

የሚመለክ ሌላ ነገር እንዲኖር አልፈልግም" በማለት ግልጽ አድርጎ ይነግረናል። እግዚአብሔር ከሕይወታችን አንዱን ክፍል ብቻ አይፈልግም። የሚፈልገው ሁለንተናችንን ነው። አምልኮታችንን ብቻ ሳይሆን፣ "የእኛ ነው" የምንለው ሁሉ የእርሱ ብቻ እንዲሆን ይፈልጋል። አሥርቱ ትዕዛዝ የሚጀምረው ታላቁን የሥነ መለኮት መመሪያ የሆነውን፣ ይኸውም "ክብር ሁሉ የእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ" የሚገልጸውን አሳብ በማወጅ ነው። እስራኤላውያን ለረጅም ዘመናት ግብጽ በቆዩበት ዘመን ግብጸውያን የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የማምለክ ዝንባሌ ስለነበራቸው፣ ወደ ጣዖት አምልኮት ብዙ ጊዜ በመሳባቸው እግዚአብሔርን እየደጋገመ ቅር ያሰኙት ነበር። በነብዩ በሕዝቄል አማካኝነት "...እንዳንዶቻችሁ ዐይኖቻችሁን ያሳረፉችሁባቸውን ርኩስ ምስሎች አስወግዱ፤ በግብጽ ጣዖታትም ራሳችሁን አታርክሱ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ" በማለት ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸው ነበር (ሕዝ. 20፡7)።

## በእኛ ሕይወት መብት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው

"እርሱ ብቻ አምላክ እንዲሆን ለእግዚአብሔር መብት የሰጠው ማን ነው?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እርሱ ብቻ መመለክ ያለበት፣ ኃያል ጌታ፣ ኃያል አምላክ የሆን ከእርሱ በቀር ሌላ ስለሌለ፣ ከማንም ፈቃድ አይጠይቅም። የመጀመሪያውን ትዕዛዝ ከመጥቀሱ በፊት እስራኤላውያንን "ከግብጽ ባርነት ያወጣሁህ እኔ ስለሆንኩ፣ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ ማምለክ የለብህም" ይላቸዋል። እግዚአብሔር ትዕዛዙን የሰጠው የእርሱን ማንነት እንዲሁም የሠራውን ታላቅ ሥራ መሠረት በማድረግ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣቸው፣ የክብሩ መግለጫ እንዲሆኑ በማሰብ ነው። የሚላቸውም "እኔ በሰማይም በምድርም ኃያል አምላክ እኔ ነኝ፤ እናንተን ለመግዛት ሥልጣንም ሆነ መብት አለኝ። ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ከእናንተ ጋር ቀደም ሲል በገባነው ቃል ኪዳን የተሣሠርን ነን። ቤዝቻችኋለሁ። ከፈርዖን እጅ ነጻ አውጥቻችኋለሁ። ዐሥር የተለያዩ መቅሰፍቶችን በማምጣት በግብጽ ያሉትን አማልክት ሁሉ ድል ነስቻለሁ፤ ኃያል አምላክ እኔ ብቻ እንደሆንኩ አሳይቻችኋለሁ። ስለዚህ አምልኮታችሁም ሆነ ምስጋናችሁ በቀጥታ ለእኔ ብቻ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በማንነቴና ባደረግኋቸው (በፈጸምኳቸው) ነገሮች ምክንያት ክብሬን



ለማናቸውም አማልክት ማካፈል አልፈልግም" ይላቸዋል። ይሁን እንጂ፣ ትዕዛዙን ስመከተል ብዙ ጊዜ ፈቃደኞች አልነበሩም።

አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ከሆነ፣ ሌሎች አማልክት ከሌሉ፣ ስለ ሌሎች አማልክት መናገር ይህን ያህል ለምን አስፈለገ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራ አንድ እግዚአብሔር (አምላክ) ብቻ እንዳለ፣ ሌሎች አማልክት ግን እውነተኛነት የሌላቸው መሆናቸውን ይናገራል። እግዚአብሔር በነብዩ ኢሳያስ አማካኝነት ስለ ራሱ ሲናገር፣ "እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ጻድቅና አዳኝ የሆነ አምላክ ከእኔ በቀር ሌላ የለም፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም" (ኢሳ. 45፥21) ይላል። ሐዋርያው ጳውሎስም ተመሳሳይ ሀሳብ ጽፏል። "...በዚህ ዓለም ጣዖት ከንቱ እንደሆነና ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እናውቃለን" ይላል (1 ቆሮ. 8፥4)። ይሄ እውነት ከሆነ "ሌላ አምላክ የለም" በማለት ለእኛ መንገሩ ምን ይጠቅማል? ብለን መልሰን መጠየቃችን አይቀርም። ሌላ አምላክ የሌለ ቢሆንም፣ እውነተኛነት የሌላቸው አማልክት በሰዎች ሕይወት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማድረግ ስለሚችሉ፣ በቅድሚያ እንዲያውቁት ለማድረግ ነው። ጳውሎስ ለገላትያ አማኞች "እግዚአብሔርን ከማወቃችሁ በፊት በባሕሪያቸው አማልክት ሳልሆኑት ባሪያዎች ነበራችሁ፤ አሁን ግን እግዚአብሔርን ዐውቃችሁታል፤ ይልቁን ደግሞ በእግዚአብሔር ታውቃችኋል። ታዲያ እንደ ገና ወደ ደካማና ወደማይጠቅም ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ? ዳግም በእርሱ በባርነት ለመጠመድ ትፈልጋላችሁን?" በማለት ያሳስባቸዋል (ገላት. 4፥8-9)።

እውነተኛነት የሌላቸው አማልክት ሰዎችን ባሪያዎች አድርገው የመግዛት ኃይል እንዳላቸው ከላይ ገልጸናል። የመጀመሪያው ትዕዛዝ የመጣው ጌታና አዳኝ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሲሆን፣ ዓላማውን ሰዎችን እውነተኛነት ከሌላቸው አማልክት ነጻ ለማድረግ ነው። ሌላ ስለ መጀመሪያው ትዕዛዝ የምንረዳው ሀሳብ ምን ይሆን? በተለይ "ከእኔ በፊት" ወይም "ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ" የሚለው ቃል ምንን ይገልጻል? እርሱን መጀመሪያ እስካደረግን ወይም እስካስቀደምን ድረስ ሌሎች አማልክትን እንድናመልክ ይፈቅዳል ማለት ይሆን? እግዚአብሔር ሁሉም ቦታ ስለሚገኝ፣ የትም ቦታ ሆነ፣ እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ፣ ከእርሱ በፊትም ሆነ በኋላ፣ ወይም ደርበን ሌሎች

ወይም ጣዖት መሆኑ ነው። ስለዚህ በሙሉ ልባችን፣ በፍጹም ነፍሳችን፣ በፍጹም ሐሳባችን የምንወደው ማን ነው? ወይም ምንድነው? "የእግዚአብሔር ወዳጅ" ተብሎ የሚጠራው አብርሃም ፍቅሩን ለሌላ ይሰጥ እንደሆን እግዚአብሔር ሊፈትነው የፈለገበት ጊዜ ነበር። "የምትወደውን አንዱን ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ ተራራ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ ሰዋው" አለው (ዘፍ. 22፥2)። አብርሃምም የቀረበለት ፈታና በጣም ከባድ ቢሆንበትም፣ ከልጁ ከይስሐቅ የበለጠ የሚወደውን እግዚአብሔር ለማስደሰትና ፈቃዱን ለመፈጸም፣ ሞርያ ተራራ ላይ የልጁን ደም ለማፍሰስ ካራውን አነሳ። ለአብርሃም ልጁ ጣዖት እንዳልሆነበት፣ እርሱን ከልጁ የበለጠ እንደሚወደው የተረዳው እግዚአብሔር፣ "ልጅህን በብላቴናው ላይ አታነርፍ ምንም ጉዳት አታድርስበት፤ አነሆ! እግዚአብሔርን እንደምትፈራ ተረድቻለሁ! ልጅህን፣ ያውም አንዱን ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አልነፈግህምና" አለው (ዘፍ. 22፥12)።

እኔና እናንተ እዕምሯችን ሥራ ሲፈታ፣ የምናስበው ምን ይሆን? ገንዘባችንን የምናጠፋው በምን ዓይነት ነገር ላይ ነው? ስሜታችንን የሚያነቃቃው፣ በጣም ደስ የሚያሰኘን ነገር ምንድነው? ማንኛውም ልባችንን ያሳረፍንበት ነገር፣ ከእግዚአብሔር የበለጠ በሕይወታችን ያስቀደምነው ነገር ጣዖታችን ሊሆን ይችላል። ልጆቻችንም ቢሆኑ፣ ከእግዚአብሔር የበለጠ በሕይወታችን ከፍተኛውን ሥፍራ የምንሰጣቸው ከሆነ፣ ጣዖቶቻችን ሊሆኑ ይችላሉ። ጣዖታችን የትኛው እንደሆን ተለይቶ የሚታወቅበት ሁለተኛው "መታመኛ" ባደረግነው፣ ወይም በምንተማመንበት ነገር ነው። እኔና እናንተ የምንታመነው በማን ወይም በምንድነው? በችግራችን ጊዜ፣ በአስቸጋሪው ሰዓት ልባችንን የምናነሳው ወደ ማን ነው? ማርቲን ሉተር "ልብህ የተጣበቀበት፣ በሙሉ ልብህ የታመንክበት፣ ያ ነገር ለአንተ አምላክህ ነው" አለ። ቶማስ ዋትሰን የተባለው መንፈሳዊ አባት ደግሞ፣ "ከእግዚአብሔር የበለጠ የምትታመንበት ነገር፣ ያ አምላክህ ይሆናል" አለ። ለደህንነታችን፣ በሕይወታችን ላይ ለሚደርሰው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እንድንታመን ተጠርተናል። ነገር ግን ከእርሱ ሌላ መታመኛችን ብናደርግ ሌላ አምላክ ማምለካችን ይሆናል።

ዛሬ እኔና እናንተ የምንታመነው በማን ይሆን? አንዳንድ ሰዎች ብቸኛ ሲሆኑ፣ አስቸጋሪ የሚመስል ነገር ሲያጋጥማቸው፣ ተስፋ ሲቆርጡ፣ ፊታቸውን ወደ መጠጥ፣ ሱስ ወደሚያስይዝ ዕጽ ወይም ድራግ፣



ወደ ሩካቤ ሥጋ ያዞራሉ። ዛሬ ሰዎች በተለያየ ነገር ይታመናሉ። ባላቸው ጥሩ ሥራ፣ ባንክ ባጠራቀሙት ገንዘብ፣ ባጠራቀሙት የጡረታ ገንዘብ፣ ባላቸው የሥራ ደረጃ፣ ባላቸው ጥሩ ቤተሰብና ዘመድ፣ ሌላው ቀርቶ በሚኖሩበት አገርም የሚታመኑ አሉ። እነዚህን ሁሉ መልካም ነገሮች እግዚአብሔር በእርሱ ከታመንን የእኛን ፍላጎት ለማሟላት ሊጠቀምባቸው ይችላል። ይሄ መሆን የሚችለው ሙሉ በሙሉ በእርሱ ብቻ ከታመንን ነው። ይሁን እንጂ፣ ብዙዎቻችን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሌሎች ነገሮችን እንድንወድና እንድንታመን እንፈተናለን። ኢዮብ በመከራው ወቅት ከእግዚአብሔር ውጪ ልቡን በምንም ነገር ላይ እንዳላሳረፈ ሲገልጽ፣ እንዲህ አለ። "ወርቅን ተስፋዬ አድርጌ፣ ወይም ንጹሑን ወርቅ 'አንተ መታመኛዬ ነህ' ብዬ ከሆነ፣ እጄ ባገኘችው ሀብት፣ በባለጠግነቴም ብዛት ደስ ብሎኝ ከሆነ፣ የፀሓይን ድምቀት አይቼ፣ ወይም የጨረቃን አካሄድ ግርማ ተመልክቼ፣ ልቤ በስውር ተታልሎ፣ ስለ ክብራቸው አፌ እጄን ስሞ ከሆነ፣ ለልዑል እግዚአብሔር ታማኝ አለመሆኔ ነውና፣ ይህም ደግሞ የሚያስቀጣኝ በደል በሆነ ነበር" ይላል (ኢዮብ 31፥24-28)።

ለእስራኤላውያን "ከእኔ በቀር ለሌሎች አማልክት አይኑርህ" የሚለውን የመጀመሪያውን ትዕዛዝ መጣስ ውለታ ቢስ መሆናቸውን ያመለክታል። ከግብጽ ባርነት ነጻ አወጣቸው። ውስን በሆነው አዕምሯቸው ሊረዱት የማይችሉት ታላላቅ ተአምራቶችን አዩ። በቀን በዳመና፣ ሌሊት በእሳት አምድ እየመራ በበረሃ ውስጥ መራቸው። "እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን" ብለው ቃል ገብተው ነበር። ይሁን እንጂ፣ "እግዚአብሔርን ቢያውቁም እንኳ፣ እንደ አምላክነቱ አላከበሩትም፤ ምስጋናም አላቀረቡለትም፤ ነገር ግን ሐሳባቸው ፍሬ ቢስ ሆነ፤ የማያስተውል ልባቸው ጨለመ" ይላል (ሮሜ 1፥21። ከነበሩበት ከባርነት ቀንበር፣ ብርቱ ከነበረው ከጠላቶቻቸው እጅ ፈልቅቆ ያወጣቸውን አምላክ ችላ ብለው እንዴት ወደ ጣዖት አምልኮት ፊታቸውን ያዞራሉ? ብለን በእስራኤላውያን መፍረዳችን አይቀርም። እኛስ ብንሆን ሕይወታችንን ጨምድዶ እስሮን ከነበረው ኃጢአት አላቆን፣ ከዘላለማዊ ሞት አውጥቶ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ያሸጋገረንን ጌታ ትተን ከእርሱ የበለጠ ሌላ ነገር በሕይወታችን እናስቀድማለን?

እስራኤላውያን እግዚአብሔር ብዙ ውለታ የዋለላቸው ቢሆንም፣ ውለታውን ለመርሳት ጊዜ አልፈጀባቸውም። እኛም ከእነርሱ ብዙ የተለየን አይደለንም። በቀላሉ እጃችንን ለሌላ አምላክ እንሰጣለን። ገንዘብ፣ ዝና፣

ክብር፣ በቀላሉ እግዚአብሔርን እንድንረሳ እንደሚያደርጉን እናውቃለን። ባል ሚስቱን ስለሚወድ ምንም ዓይነት ወንድ የሚስቱን ፍቅር እንዲጋራው የሚፈልግ የለም። ሚስት ባሏን፣ "አንተንም፣ ...እከሌንም በጣም እወዳችኋለሁ..." ብትለው፣ አዕምሮውን ያመመው ካልሆነ በቀር "እኔን እስከወደድሽኝ ድረስ፣ እከሌንም ብትወጂው ግድ የለኝም" የሚል ባል በዚህ ዓለም ውስጥ ይኖራል ብለን እናምንም። ዛሬ በየትኛውም ዓለም፣ በባሏ ላይ ደርባ ሌላ ወንድ የምትወደውን ሴት፣ አጥፍተው የሚጠፉ ወንዶች እንዳሉ የታወቀ ነው። እግዚአብሔርም ባል ሚስቱን ከሚወደው የበለጠ ሕዝቡን በጣም ይወዳል። ስለሆነም ፍቅሩን ለሌላ አምላክ ማካፈል እንደማይፈልግ በጣም ግልጽ በሆነ ቋንቋ ደጋግሞ ይናገራል። *"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ"* በማለት ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥቶናል (የማቴ. 22፥37)። "እኔን እስከ ወደድከኝ ድረስ ሌሎችን አማልክት ብትወድ ግድ የለኝም" አይልም።

እስራኤላውያን ይህን የመጀመሪያውን ትዕዛዝ በሚያፈርሱበት ጊዜ በተደጋጋሚ ይደርስባቸው የነበረውን ጥፋትና መከራ እናስታውሳለን። በአንድ ወቅት እስራኤላውያን ሌሎች አማልክቶችን በመከተላቸው በፍልስጥኤማውያን ታላቅ መሸነፍ ደርሶባቸው ልባቸው በሀዘን ተሞልቶ እግዚአብሔርን መፈለግ ሲጀምሩ ሳሙኤል እንዲህ አላቸው። *"በፍጹም ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር የምትመለሱ ከሆነ ሌሎችን አማልክትና አስታሮትን ከመካከላችሁ አስወግዱ፤ ራሳችሁንም ለእግዚአብሔር አሳልፋችሁ ስጡ እርሱንም ብቻ አምልኩ፤ እርሱም ከፍልስጥኤማውያን እጅ ይታደጋችኋል"* አላቸው (1 ሳሙ. 7፥3)። ዛሬም እኔና እናንተ በሕይወታችን የምናስቀድማቸው፣ ከእግዚአብሔር የበለጠ የምንወዳቸው ነገሮች ምን ይሆኑ? ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር እነዚያ ነገሮች መልካም ነገሮች እንኳን ቢሆኑ፣ የመጀመሪያውን ሥፍራ የምንሰጣቸው ከሆነ፣ "እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ" ስለሆነ፣ በዚያ ደስ አይለውም። የግል ሕይወታችንን በጥንቃቄ እንመርምር። ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን!



# ምዕራፍ አራት

## ሁለተኛው ትዕዛዝ

## ሌሎች አማልክትን ደርባችሁ አታምልኩ

"...በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ
አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም።"
(ዘፀአት 20፥4-5)

ከዐሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ሦስቱ የመጀመሪያዎቹ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት፣ ወይም በቀጥታ የሕጉ ባለቤት የሆነውን ጌታ የሚመለከት ሲሆን፣ የተቀሩት ሰውን በግልም ሆነ እርስ በርሱ ስላለው ግንኙነት መመሪያ የሚሰጥ ነው። *"ከእኔ በቀር ለሌሎች አማልክት አይኑርህ"* የሚለው የመጀመሪያው ትዕዛዝና እንዲሁም *"...በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤"* የሚለው ሁለተኛው ትዕዛዝ፣ አንድ ዓይነት ይምሰሉ እንጂ፥ የተለያዩ ናቸው። የመጀመሪያው ትዕዛዝ፣ እውነተኛውን አምላክን እውነተኛ ካልሆነው አምላክ

ጋር ደባልቀን ማምለክ ስለማንችል፣ አንዱን የግድ መምረጥ አለብን፣ እውነተኛውን አምላክ ለማምለክ ምርጫችን ከሆነ ደግሞ፣ ሌሎች አማልክትን ከሕይወታችን የግድ ማስወገድ እንዳለብን መመሪያ የሚሰጥ ነው። ሁለተኛው ትዕዛዝ ግን ትክክለኛውን አምላክ በትክክል ወይም በአግባቡ እንድናመልክ የሚያዝ ነው። ጣዖት በሚመለክበት ዓይነትና ሁኔታ እንዲመለክ እግዚአብሔር አይፈልም። "እርሱን እስካመለክነው ድረስ በየትኛውም ዓይነት ሁኔታ ብናመልከው ምን አለበት?" ብለው የሚጠይቁ እንደማይጠፉ እርግጠኞች ነን። በምን ዓይነት መንገድ መመለክ እንደሚፈልግ ቃሉ ግልጽ ባለ ሁኔታ ይነግረናል። "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል" ይላል (ዮሐ. 4፥24)። እግዚአብሔር ትክክል ባልሆነ ሁኔታ እንድናመልከው ስለማይፈልግ ነው "በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ አትስገድላቸውም" በማለት ሁለተኛውን ትዕዛዝ የሰጠን።

## በአንደኛውና በሁለተኛው ትዕዛዝ መካከል ያለው ልዩነት

በነዚህ በሁለት ትዕዛዞች መካከል ያለውን ልዩነት የበለጠ ለመረዳት፣ ብሉይ ኪዳን ውስጥ "ኢዩ"የተባለውን ሰው ታሪክ መመልከቱ ይጠቅማል። ኢዩ የበአል አምልኮት በእስራኤል ውስጥ በጣም እንዲስፋፋ ምክንያት የነበረችውን፣ የእግዚአብሔርን ነብያት ሰብስባ በሰይፍ ያስገደለችውን፣ የአካብን ሚስት፣ ኤልዛቢልን በሞት የቀጣ ሰው ነው። ኢዩ ኤልዛቤል ከፎቅ ተወርውራ እንድትገደል ካደረገ በኋላ፣ እርሷ ነብያትን እንዳስገደለች፣ እርሱም የበአልን ነብያት በአንድ ላይ ሰብስቦ በሰይፍ አስገደለ። ከድንጋይ የተሠሩትን ማምለኪያ ምስሎች ከበአል ቤተ ጣዖት ወጥቶ እንዲቃጠል አደረገ። የበአልን ማምለኪያ ምስል ቀጠቀጠ፤ የበአልንም ቤተ አምልኮ አፈረሰ፤ በዚህ ሁኔታ የባዕድ አምልኮን ከእስራኤል ምድር አስወገደ (2 ነገ. 10)። እስከዚህ ድረስ ኢዩ መልካም የሆነውን ነገር፣ ልክ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው አደረገ።

በሌላ በኩል ግን፣ ኢዮ ያበላሸው አንድ ነገር እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። "...ኢዩ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም፣ በቤቴልና በዳን የወርቅ ጥጃዎች እንዲያመልኩ እስራኤልንካሳተበት ኃጢአት አልራቀም" ይላል (2 ነገ. 10፥29)። ኢዩ ያደረጋቸው መልካም ነገሮች ቢኖሩም፣ እግዚአብሔር



ሙሉ በሙሉ የተደሰተበት ሰው እንዳልነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "እግዚአብሔር ኢዩን 'በፊቴ መልካም የሆነውን ነገር ስላደረግህና በአክዓብም ቤት ላይ እንዲደርስ በልቤ ያለውን ሁሉ ስለፈጸምህ፣ ዘርህ እስከ አራት ትውልድ ድረስ በእስራኤል ዙፋን ላይ ይቀመጣል' አለው። ነገር ግን ኢዩ የእስራኤልን አምላክ የእግዚአብሔርን ሕግ በፍጹም ልቡ ለመጠበቅ ጥንቃቄ አላደረገም፤ ኢዮርብዓም፣ እስራኤልን ካሳተበት ኃጢአት አልራቀምና" ይላል (2 ነገ. 10፥30-31)። ኢዩ የበአልን አምልኮ በፍጹም ከእስራኤል ካስወገደ፣ ታዲያ እነዚህ የወርቅ ጥጃዎች በእስራኤል ውስጥ ምን ያደርጋሉ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ኢዩ "ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አይኑርህ" የሚለውን የመጀመሪያውን ትዕዛዝ ሲያስፈጽም፣ ሁለተኛውን ትዕዛዝ፣ "...በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤" የሚለውን ግን ሰዎች ሲጥሱ እያየ አላስቆማቸውም። የወርቅ ጥጃዎችን የሚያመልኳቸውና የሚሰግዱላቸው፣ እንደ ባዕድ አምልኮት ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ እንደ መሣሪያ አድርገው የተጠቀሙበት ነበር። እግዚአብሔር ግን በዚያን ዓይነት መንገድ እንዲመለክ ስለማይፈልግ ነው ሁለተኛውን ትዕዛዝ የሰጣቸው።

ሁለተኛው ትዕዛዝ ከሌሎቹ ትዕዛዛት ሁሉ የበለጠ ረጅም (ሰፊ) ነው። "በላይ በሰማይ ወይም በታች በምድር ካለው ወይም በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች፣ በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ የሚጠሉኝን ልጆች ከአባቶቻቸው ኃጢአት የተነሣ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የምቀጣ ቀናተኛ አምላክ ነኝ፤ ነገር ግን ለሚወዱኝና ትእዛዛቴን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ፍቅርን የማሳይ ነኝ" (ዘፀአት 20፥4-6) ይላል። ይሄን ትዕዛዝ (ሕግ) ለመረዳት ይህን ያህል ከባድ አይደለም። ባጭሩ "ምስል ወይም ቅርጽ ሠርተህ አታምልከኝ" ማለቱ ነው።

በወርቅ፣ በብረት፣ በድንጋይ ወይም በእንጨት የሚሠሩ ሀውልቶችም ሆኑ ቅርጻ ቅርጾች መልክ የሚያወጣላቸው፣ የሚቀርጻቸው፣ የሰው እጅ እንደ ሆነ ግልጽ ነው። ተፈጣሪ የሆነው ሰው "መለኮታዊ" የሆነውን ነገር እንዴት መሥራት ይችላል? ስለዚህ ተፈጣሪ በሆነው በሰው እጅ ተቀጥቅጦ በሚሠራ ቁስ አካላዊ በሆነ ነገር እንዲመለክ እግዚአብሔር ስለማይፈልግ ነው ሁለተኛውን ሕግ ለሰው ልጅ የሰጠው። ይሄም ሕግ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን እውነተኛ ፍቅር ያሳያል እንጂ፣ ደስ እንዳይለን ነጻነ

ታችንን ለመከልከል አይደለም። እግዚአብሔር እኛን እንደወደደን እኛም እርሱን እንድንወደው ይፈልጋል። ፍቅራችንንም የምንገልጸው ሌሎች አማልክትን ወደ ሕይወታችን ሳናስገባ፣ የሚገባውን ክብር ለእርሱ ብቻ በመስጠት ስናመልከው ነው። የምናመልከውም በእውነትና በመንፈስ እንጂ፣ ቅርጻ ቅርጽ ሠርተን አይደለም"። ዘዳግም 16፥22 ላይ "አምላክህ እግዚአብሔር የሚጠላውን ማምለኪያ ዐምድ ለአንተ አታቁም" በማለት በግልጽ ያዘናል።

በየቤተ ክርስቲያኑ የተለያዩ ምስሎችና ቅርጻ ቅርጾች መድረኩ ላይና እንዲሁም ከመድረኩ ውጪ እናያለን። መድረኩ ላይ በእንጨት፣ በብረት፣ በነሃስ ወይም በወርቅ የተሠራ መስቀል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የያዙ ባንዲራዎች ተንጠልጥለው ይታያሉ። የክርስቶስ ስዕል ግድግዳው ላይ ተሰቅሎ ይታያል። እንዲሁም አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይም ውጪ በድንጋይ ላይ የተቀረጸ አሥርቱ ትዕዛዛትን የያዘ ሀውልት ይገኛል። እነዚህ ሥዕሎችና ቅርጻ ቅርጾች "ጣዖታት" ናቸው? እነዚህን ቤተ ክርስቲያኖችን ውስጥ እንዲገኙ ማድረግ ሁለተኛውን ትዕዛዝ (ሕግ) አፍርሰን ጣዖት ማምለካችን ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ከላይ የገለጽናቸው ነገሮች እንደ ጣዖት የምንቆጥራቸው ከሆነ፣ እነዚህን ምስሎች ከቤተ ክርስቲያናችን እንዲያስወጡልን የቤተ ክርስቲያን መሪዎቻችንን መጠየቃችን አይቀርም ነበር። ከላይ የገለጽናቸው ምስሎችና ቅርጻ ቅርጾችን እግዚአብሔርን ለማምለክ ወይም ለማክበር ብሎ ማንም ተንበርክኮ ስለማይሰግድላቸው እንደ "ጣዖት" ሊታዩ አይገባም። ለስዕሎቹ ወይም ለቅርጻ ቅርጾቹ ተንበርክኮ የሚሰግድ ሰው ቢኖር ግን፣ እነዚያ ቅርጻ ቅርጾች ለዚያ ሰው ጣዖት መሆናቸው ግልጽ ነው። በዚያ ዓይነት መልክና ሁኔታ እንዳናመልከው ነው እግዚአብሔር ሁለተኛውን ትዕዛዝ የሰጠን።

## ጣዖት በእጅ የተሠራ ቁስ አካል ብቻ አይደለም

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክቱ ፈጣሪውን ትተው ተፈጣሪውን ስለሚያመልኩት ሰዎች ሲጽፍ፣ "የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ለወጡ፤ በፈጣሪ ፈንታ ፍጡር አመለኩ፤ አገለገሉም" ይላል (ሮሜ 1፥25)። እኔና እናንተ እግዚአብሔር ብቻ ሊገዛው (ሊቆጣጠረው) የሚገባውን ሕይወታችንን፣ ሌላ ነገር እንዲገዛው የምንፈቅድ ከሆነ፣ ያ ነገር በልባችን ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ እንዲይዝ ከፈቀድን፣ እግዚአብሔር ብቻ መቀመጥ በሚገባው በሕይወታችን ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ ካደረግን፣ ያ ነገር በእጅ የተሠራ ቅርጽ ባይሆንም ጣዖታችን ወይም አምላካችን እንደሆነ ግልጽ ነው። ማንኛውም ቁስ አካል የሆነ ነገር እኛ እንድንገለገልበት ወይም እንድንጠቀምበት ተብሎ የተሠራ እንጂ፣ ሕይወታችንን የሚቆጣጠር፣ የምናመልከው አምላካችን እንዲሆን አይደለም። መልካምና በጎ የሆኑ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር የፈጠራቸው፣ እኔና እናንተ በአግባቡ እንድንጠቀምባቸው ወይም እንድንገለገልባቸው እንጂ፣ እንድናመልካቸው፣ በቁጥጥራቸው ሥር እንዲያደርጉን አይደለም።

ሰው ጣዖትን ከፈለገው ነገር ውስጥ የመፍጠር ወይም የማበጀት ችሎታና ዝንባሌ እንዳለው የታወቀ ነው። ለምሳሌ የቤት እመቤት ቤቷን በንጽህና፣ በሚያምር መልክ አሳምራ ብትይዝ ትደነቃለች እንጂ፣ አትወቀስም። የሚያማምሩ ብርጭቆዎቿና ጌጣ ጌጥ ያላቸው የሳህኖቿ አደራደር፣ ወይም አቀማመጥ፣ የአገር ባህል ዕቃዎቿ በአማረ ሁኔታ ሥፍራ-ሥፍራቸውን መያዛቸው፣ ግድግዳው ላይ ያንጠለጠለቻቸው ልዩ ልዩ የሚያማምሩ ሥዕሎች የሰው ዓይን የሚስቡና ደስ የሚያሰኙ በመሆናቸው ባለሞያ ተብላ ትደነቃለች እንጂ፣ "የቤት ዕቃዎቿ ጣዖት የሆኑባት ሴት ነች" በማለት የሚወቅሳት ወይም የሚታዘብት ሰው ይኖራል ብለን አናምንም። ይሁን እንጂ ሲኒው፣ ብርጭቆው የማይጠጣበት፣ ሳህኑ ከዓመት ዓመት አንድ ጊዜም ቢሆን ቤተሰቡም ሆነ እንግዶች የማይገለገሉበት ቢሆን፣ ድንገት ከልጆቿ አንዱ ሳያውቅ አንድ ብርጭቆ ወይም ሳህን ቢሰብር፣ ዓለም በላዩዋ ላይ እንደተደፋባት ሆኖ ተሰምቷት ሞራሉን የሚሰብር ስድብ በልጁ ላይ ብታወርድበት፣ ዕቃዋ ጣዖቷ እንደሆነ ያሳያል።

ያማረው ፎቴዋ እንዳይቆሸሽ በማለት ሰው እንዳይቀመጥበት፣ ልጆቿ ሳሎን እንዳይገቡ ብታደርግ፣ ገብተው ከተገኙ ግን የሚደበደቡ፣ ወይም የስድብ መዓት የሚወርድባቸው ከሆነ፣ ቤተሰቡ ቤቱን እንደ ቤቱ አድርጎ በመውሰድ እንዳይዝናናበት፣ እንዳይደሰትበት፣ በአጠቃላይ ነጻነቱን የሚያጣበት ከሆነ፣ እንደ ኤግዚቢሽን እንዲታይ ብቻ ተከልሎ የሚቀመጥ ከሆነ፣ ለዚያች ሴት እነዚያ የደረደረቻቸው ዕቃዎች መገልገያ ሳይሆኑ ጣዖቶቿ ናቸው። እርሷና ቤተሰቧ እንዲገለገሉበት የተሠሩትን ዕቃዎች

ጎንበስ ብላ ባትስግድላቸውም፣ በውስጧ ግን እያመሰከቻቸው እንደሆነ
ግልጽ ነው። ከልጆቿና ከቤተሰቧ ደስታ ይልቅ፣ "...ቤትሽ እንዴት
ያምራል?" መባልን የምታስቀድም ነች። የምትቀናው ለልጆቿ ወይም
ለቤተሰቧ ምቾት ሳይሆን፣ ለፎቴው፣ ለብርጭቆው፣ ለሲኒው፣ ለሳህኑና
እነዚህን ለመሳሰሉት ነገሮች፣ እንዲሁም ከሰዎች ለሚሰጣት አድናቆት
ብቻ ነው። ዕቃዎቿ ጣዖት የሆኑባት የቤት እመቤት፣ ከልጆቿ መካከል
አንዱ ሳያውቅ አንድ ነገር ፎቴው ላይ ድንገት ጠብ ቢያደርግ የምታደር
ስበት ዕርግማን፣ የሚታሳርፍበት ዱላ ፍጹም ሌላ ነው። ቤትን በንጽህና
መያዝ መጥፎ ነው ማለታችን እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በአግባቡ መጠቀ
ምና፣ ሳይጠቀሙበት ሲገቡና ሲወጡ እያዩ ማለፍ ወይም መሳለም ልዩነት
አለው። ከላይ የገለጽናት ሴት፣ ብርጭቆዎቿና ሳህኖቿ መጠቀሚያ፣
መገልገያ ዕቅዎች ከመሆን ይልቅ ጣዖቶቿ፣ አምላኮቿ እንዳደረገቻቸው
ግልጽ ነው።

"ብዙ ቢኖረኝ፣ የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ ባገኝ፣ በጣም ደስተኛ
እሆናለሁ" ብለው የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች አሉ። በሰለጠነው ዓለም
ዕቃቸውን ለመሸጥ በተለያየ መንገድ ማስታወቂያ የሚያወጡ ነጋዴዎች፣
ለመሸጥ የሚሞክሩት ዕቃዎችን ሳይሆን "ደስታን" ለመሸጥ ይመስላል።
"ይህንና ያንን ዕቃ ብትገዙ፣ ይሄና ያ ቢኖራችሁ፣ ከዚህ በፊት ቀምሳች
ሁት የማታውቁትን ዓይነት ልዩ ደስታን ታገኛላችሁ" በማለት ልዩ ልዩ
ዘዴ በመጠቀም ገበያተኞቻቸውን ያባብላሉ። በቴሌቪዥንም ሆነ በተለ
ያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች ማስታወቂያ የሚያወጡት ቆሳቁሳዊ ነገሮችን
ለመሸጥ ሳይሆን፣ ደስታን ለሚፈልጉ ሰዎች "ደስታን" ለመሸጥ ነው።
"ይህን ዓይነት መኪና፣ ይህን ዓይነት ልብስ፣ ይህን ዓይነት ጌጣ ጌጥ...
ይህን ዓይነት የቤት ዕቃዎች... ብትገዙ ደስታችሁ እጥፍ ድርብ ይሆናሉ"
ይሉናል። እርግጥ ነው እነዚህን መልካም ነገሮችን ማግኘት ደስታን ይሰ
ጣል። እውነቱ ግን የሚሰጡን ደስታ ዘላቂነት ያለው ሳይሆን ጊዜያዊ፣
ወይም ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ይህን እውነት የሚረዱት ሰዎች በጣም
የተወሰኑ ናቸው።

ከልጆቼ መካከል ሙሴ፣ ቆሳቁሳዊ ነገር፣ ውድ የሆነ ዕቃ፣ በጣም
ይወዳል። አንድ ጊዜ በፕሮግራማችን መሠረት ከአንድ ሆቴል ቤት ቁርስ
ለመብላት ተገናኘን። ስለ ሥራውና በሳምንቱ ውስጥ ስላጋጠሙት አንዳ
ንድ ሁኔታዎች ካወራን በኋላ፣ በልቡ ውስጥ የሚመላለሰውን ነገር አጫወ



ተኝ። መጀመሪያ ላይ "ይህቺ መኪናዬ እየተበላሸች ብዙ ገንዘብ እያስወጣ
ችኝ ነው... በቀደም ዕለት ይሄና ያ ተበላሽቶ፣ ይህን ያህል ገንዘብ አወ
ጣሁ... አሁን ደግሞ እንዲህ ዓይነት ችግር አለባት..." አለኝ። የሙሴን
ጠባይ ስለማውቅ፣ ይሄን የሚነግረኝ ነገር ለመንደርደሪያ እንጂ፣ ችግሩን
ለማውራት ፈልጎ እንዳልሆነ አውቃለሁ። እንደ ገመትኩትም፣ ፈገግ
ብሎ "አንድ ግሩም መኪና አየሁ... ሞዴሏ እንዲህ ዓይነት ነች... እምወደ
ውን ዓይነት ቀለም ያላት ናት... በቅድሚያ ምንም አልከፍልም... ገንዘ
ቡን ከባንክ ለመበደር የሚከፈለው ወለድ ከመቶ አንድ ብቻ ነው..." ብሎ
አለማምሮ ነገረኝ። የመኪናውን ዋጋ ሲሰማ ይደነግጣል ብሎ አልነገረ
ኝም። እኔም በደንብ ካዳመጥኩት በኋላ "ዋጋዋ ስንት ነው?" ብዬ ጠየቅሁ።
እየሳቀና እየፈራ "ይህን ያህል ነው... መኪናዋን በጣም ስለወደድኳት ጥሩ
ዋጋ ነው ብዬ አምናለሁ" ካለኝ በኋላ መኪናዋን እንድወዳት ለማድረግ
ሌሎች ነገሮችንም ጨማምሮ ነገረኝ። የገንዘቡ ብዛት ስላስደነገጠኝ፣
"ይህን ያህል ገንዘብ የምታወጣ ከሆነ ቤት ለምን አትገዛበትም" ብዬ
ጠየቅሁት። ሙሴ የሚያባብለኝ፣ "ጥሩ ነው! ግዛው!" እንድለው፣ ከእርሱ
አሳብ ጋር እንድስማማለት ብቻ ነው። እኔም ቢሰማኝም ባይሰማኝም
"ሙሴ አብደሃል?" አልኩት። የፈቀደውን ለመወሰን ሙሉ መብትና ነጻ
ነት ስላለው የእኔን ፈቃድ መጠየቅ ስለሌበት በማግሥቱ ሄዶ አዲሷን
መኪና አወጣ።

ከአንድ ሳምንት በኋላ አዲሱን መኪናውን ሊያሳየኝ ቢሮ መጣ።
እያደነቀ ነገረኝ። ሦስት አራት ቀን ከነዳት በኋላ፣ ለመኪናዋ የነበረው
አምሮት ሲሰክን፣ ወይም መኪናዋን ቶሎ ሲጠግባት፣ ዐይኖቹ ተከፍተው
አንዳንድ ነገሮችን ማየት ጀመረ። በጣም ግልጽ ልጅ ስለሆነ፣ ስሜቱን
አልደበቀኝም። "አንድ ቀን ከነዳኋት በኋላ፣ ደስታዬ አበቃ... አሁን ምንም
አይመስለኝም... አሁን የሚታየኝ የምታስወጣኝ ወጪ ነው። መኪናዋ
በጣም ውድ ስለሆነች፣ አንድ ጎማ ብቻ ለመቀየር ብፈልግ ስንት እንደሚ
ጠይቀኝ ታውቃለህ?... 4 መቶ ዶለር ነው" አለኝ። ደስታዬ በአንድ ቀን
ብቻ ያበቃል ብዬ አላሰብኩም ነበር" አለኝ። እኔም፣ "በል እንግዲህ፣
የዚህችን መኪና ዋጋ ከፍለህ እስክትጨርስ ድረስ የመኪናዋ ባርያ ሆነህ
ትቆያለህ። ገንዘቡን ከፍለህ እስክትጨርስ ድረስ፣ ለሚቀጥሉት አምስት
ዓመታት ምንም ዓይነት የዕድገት ዕቅድ ማውጣት አትችልም" አልኩት።
በዕድሜያቸው እንደ ሙሴ ልጅ ባይሆኑም፣ የሙሴን ዓይነት ጠባይ ያላ

ቸው፣ ቁሳቁሳዊ ነገሮች ጣዖት የሆነባቸው ብዙ ሰዎች አሉ። ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ፣ ክርስቲያኖችም ናቸው። ኸርበርት ሽሎስበርግ የተባሉት ጸሐፊ "አይድል ፎር ዲስትራክሺን" (አጥፊ የሆኑ ጣዖታት) በሚለው መጽሐፋቸው፣

"ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑ እውነተኛ ነገሮችን፣ ይኸውም ምግብ፣ መጠጥ፣ መጠለያ፣ ከመጥገብ ወይም ከመርካት ደረጃ ማድረስ ይቻላል። ትክክለኛነት የሌላቸው (ዲቃላ የሆኑ ፍላጎቶች)፣ ይኸውም ትዕቢት፣ ቅናት፣ ስግብግብነት፣--እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፍላጎቶችን ግን፣ ምንጊዜም ቢሆን ማርካት አይቻልም። እነዚህ ቁስ አካላዊ ነገሮች ለሰው ልጅ እንደ እንቅልፍ ኪኒን ብቻ ናቸው። በቂ ነው የሚባል ነገር የለም" አሉ።

እኔና እናንተ ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፣ ቁሳቁሳዊ ነገሮች ላይ ትኩረት መስጠት፣ ሲጠማን የጨው ውሃ እንደ መጠጣት ዓይነት ነው። የጨው ውሃ በጠማነው ቁጥር የበለጠ ይጠማናል። ልክ እንደዚሁም ቁሳቁሳዊ ነገር፣ ባገኘን ቁጥር በመርካት ፈንታ ሌላ ያላገኘነውን እንፈልጋለን። "እሁን ቀደም ሲል ከነበረን የበለጠ ብናገኝ ፈጽሞ የማንረካ መሆናችንን ብቻ ሳይሆን፣ የበለጠ ደስተኞች እንዳንሆን የሚያደርገን መሆኑ ነው። ሰዎች "ደሞዜ ይህን ያህል ቢሆን ኖሮ ፍላጎቴ ተሟልቶ ደስተኛ እሆን ነበር" ይላሉ። ከተመኙት ደረጃ ሲደርሱ ወይም ካሰቡት በላይ ከፍተኛ ደሞዝ ቢያገኙም፣ ቀደም ሲል ይኖረኛል ብለው ያሰቡት ደስታ ሳያገኙት ህልም ብቻ ሆኖ ይቀራል። "አንድ ሰው ምን ያህል ብር ቢያገኝ ነው ይበቃኛል ብሎ ደስ የሚለው" ለሚለው ጥያቄ አንድ አስተዋይ የሆኑ ሰው ሲመልሱ፣ "ሰው የሚበቃኝን አግኝቻለሁ የሚለው፣ እሁን ካለው ትንሽ የበለጠ ያገኘ እንደሆነ ነው" አሉ። ምን ማለታቸው ነው፣ "የበለጠ" ሲያገኝ፣ እንደገና የበለጠ ስለሚፈልግ ምንጊዜም በቃኝ አይልም ማለታቸው ነው።

በዚህ ዓይነት ደስታ የምናጣበት አንደኛው ምክንያት የቁስ አካል በብዛት ሲኖረን ነው። ጣዖት የሆነብን የቁስ አካል አስተሳሰባችንን የሚያበላሽብን፣ በቁስ አካል ብዛት ደስታ እናገኛለን ማለታችን ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች ሁሉ የተሻልን እንሆናለን ብለን ማሰባችን ጭምር ነው። "አለን" በምንለው፣ በጨበጥነው ነገር፣ ለራሳችን ያለንን ዋጋ ለመተመን እንፈልጋለን። ብዙ የቁስ አካል ያላቸው፣ ከእኛ ብዙ ነገር ከሌለን ሰዎች ይበልጣሉ... ይሻላሉ" ብለን በአዕምሯችን ውስጥ እንስላቸዋለን። ስለዚህ የማያስፈልገን ነገር ቢሆንም እንኳን፣ ብዙ ገንዘብ፣ ብዙ ቁሳቁሳዊ ነገር ቢኖረን የበለጠ ተቀባይነት የሚያስገኝልን፣ ደስታችንን የሚጨምርልን ይመስለንና ያ ነገር ጣዖት እስኪሆንብን ድረስ በሕይወታችን ከፍተኛውን ሥፍራ እንሰጠዋለን። እውነቱ ግን እንደምናስበው የበለጠ ደስተኞች እያደርገንም፤ ከሌሎች የተሻልንና የበለጥንም አንሆንም።



ይህንን እውነት የሚያውቀው ጌታ ኢየሱስ "የሰው ሕይወቱ በሀብቱ ብዛት የተመሠረተ ስላልሆነ፣ ተጠንቀቁ፤ ከስግብግብነትም ሁሉ ራሳችሁን ጠብቁ" በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናል (የሉቃ. 12፥15)። የሚያሳዝነው፣ አንዳንድ ሰዎች ባላቸው ሀብትና ታዋቂነት የሚታመኑ መሆናቸው ነው። ስለሞንም ይህን እውነት ሲገልጽ፣ "የባለጠጎች ሀብት የተመሸገ ከተማቸው ነው፤ እንደማይወጣ ረጅም ግንብም ይቆጥሩታል" ይላል (ምሳሌ 18፥11)። እንግዲህ ብዙ ገንዘብ፣ ቤት፣ መኪና፣ ልብስ፣ ጌጣ ጌጥ ቢኖረንና ከእነርሱ መላቀቅ ቢያቅተን፣ እነዚህ ቁሳቁሳዊ ነገሮች "የእኛ ናቸው" በማለት ፈንታ፣ ሕይወት የሌላቸው ቢሆኑም እንኳ "እኛ የእነርሱ" ነን፤ እኛ በእነርሱ ላይ ከሚኖረን የበለጠ፣ እነርሱ በእኛ ላይ ኃይል አላቸው። ሕይወታችንን የሚገዙት እነርሱ ናቸው። እውነቱን እንዳለ በግልጽ የሚያሳየን ከእግዚአብሔር ቃል የተሻለ ይኖረናል ብለን አናምንም። "...ትርፍ ነገር ለማግኘት ከመቅበዝበዝ ይልቅ፣ ባለህ ነገር መደሰት የተሻለ ነው" ይላል (መክብ. 6፥9)። የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈው ሰው ደግሞ "ራሳችሁን ከፍቅረ ንዋይ ጠብቁ፤ ባላችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር 'ከቶ አልተውህም፤ በፍጹም አልጥልህም' ብሎአል" ይለናል (ዕብ. 13፥5)። እንግዲህ በሕይወታችን ጣዖት የሆኑብን ቁሳቁሳዊ ነገሮች፣ ወይም ምድራዊ የሆኑ ነገሮች ይሆኑ? እነ እከሌ ያገኙትን ካላገኘን፣ እነ እከሌ ከደረሱበት ካልደረስን በማለት ነፍሳችን ቀንና ማታ በነዚህ ፍላጎቶች ተሞልታ ትጨነቃለች? ሐዋርያው ጳውሎስ ቆላ. 3፥2 ላይ "ዘወትር በላይ በሰማይ ስላሉት ነገሮች አስቡ እንጂ በምድር ላይ ስላሉት ነገሮች አታስቡ" በማለት የሰጠንን ምክር አጥብቀን እንያዝ።

"...በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም" ሚለው ሁለተኛው ትዕዛዝ ይህን ዓይነት መንፈስ የያዘ ነው። "እኔ ብቻ አምላክህ ነኝ፤ አዳኝህ ነኝ፤ ብዙ ዋጋ ከፍዬ ከሞት የዋጀ

*ሁሀ እኔ ነኝ፤ ለእኔ የሚገባውን ሥፍራ በምንም ዓይነት ለሌላ አምላክ እንድትሰጥ አልፈልግም፤ በጣም ከልቤ እወድሃለሁ፤ ሁልጊዜ ልጠነቀቅልህ፣ ከለላ ልሆንልህ፣ ልባርክህ እፈጋለሁ። በጣም ስለምወድህ በሕይወትህ ሌላ አምላክ እታስገባ፤ አምላክህ እኔ ብቻ ልሁን"* ማለቱ ነው። ከማንኛውም ነገር የበለጠ ይሄን ፍቅር የሆነውን ጌታ ብንወደው፣ በሕይወታችን ውስጥ ቅድሚያ ብንሰጠው፣ ለእርሱ ይበዛበት ይሆን? አምላካችን፣ የሕይወታችን ገዢ ስለሆነ፣ እኛን ከሞት ለማዳን ብዙ ዋጋ የከፈለልን በመሆኑ ያንስበት እንደሆን እንጂ አይበዛበትም። እግዚአብሔር ይህንን ሕግ (ትዕዛዝ) ሲሰጠን ዋና ዓላማው መንገዳችንን ጠባብና አስቸጋሪ ለማድረግ፣ ደስታችንን ለመቀነስ አይደለም። በሙሉ ልባችን፣ በሙሉ ነፍሳችንና ኃይላችን እርሱን እስመውደድ፣ ከእርሱ ጋር በጣም የተቀራረበ ግንኙነት አለማድረግ የሚያደርስብንን ጉዳት ስለሚያውቅ ነው። ሚስትም ሆነች ባል በኑሮ ጓደኛቸው ሕይወት ውስጥ ሌላ ሰው እንዲኖር እንደማይፈልጉት ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ይህንን ሕግ የሰጠን በሕይወታችን ሌላ አምላክ እንዲኖረን የማይፈልግ መሆኑን ሊገልጽልን ነው።

ከጌታ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ተጀምሮ የሚያቆም ሳይሆን እስከ ሕይወታችን መጨረሻ ድረስ የሚዘልቅ ነው። ከእርሱ ጋር ያለን ቃልኪዳናችን ዘለዓለማዊና የጠበቀ ነው። እግዚአብሔር የሚያየው አጥብቆ ስለሆነ፣ የሚለን "በእኔና በእናንተ መካከል ምንም ነገር አታስገቡ። በልባችሁ ውስጥ ምንም ዓይነት ጣዖት አታስቀምጡ። ስእኔ የሚገባውን ሥፍራ ለሌላ አምላክ አትስጡ" ማለቱ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ በመጨረሻው ዕድሜ ላይ ሲደርስ፣ "ልጆቼ ሆይ! ራሳችሁን ከጣዖቶች ጠብቁ በማለት ያስጠነቅቀናል። እነዚህ ጣዖቶች ምንድናቸው? በእንጨት፣ በብረት፣ በነሐስ፣ በወርቅና በመሳሰሉት ነገሮች የሚሠሩ ቅርጾች ብቻ አይደሉም። በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን፣ ሳይንስና ሥልጣኔ በበዛበት ዓለም ውስጥ ከላይ በገለጽናቸው ነገሮች የተሠሩትን ምስል እንደ አምላክ አድርገው የሚሰግዱ ይኖራሉ ብለን ለማመን ከባድ ይሆንብናል። ቀሳቁሳዊ አይሁኑ እንጂ፣ ብዙ ጣዖት አምላኪዎች በዓለማችን እንዳሉ አንጠራጠርም።



## የግል ጥያት ይኖረን ይሆን?

ቀደም ሲል እንደገለጽነው ለአንዳንዶች ጣዖታቸው "ገንዘብ" ይሆናል። እግዚአብሔርን ከሕይወታቸው ባያስወጡትም፣ ገንዘብንና እግዚአብሔርን በልባቸው ውስጥ እኩል ሥፍራ ሰጥተው ሁለቱንም ለማስተናገድ የሚፈልጉ ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። ጣዖትንና እግዚአብሔርን በአንድ ላይ ይዞ ማስተናገድ እንደማይችል ኤልያስ በቃርሜሎስ ተራራ ላይ ለእስራኤል ሕዝብ በሚገባቸው ቋንቋ ተናግሯል። እግዚአብሔርንና በአልን በአንድ ላይ ማስተናገድ ወይም መያዝ እንደማይቻል በሕዝቡ ፊት ቀርቦ ሲገልጽ፣ *"በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉት እስከ መቼ ድረስ ነው? አምላክ እግዚአብሔር ከሆነ እግዚአብሔርን ተከተሉ፤ በአል አምላክ ከሆነም በአልን ተከተሉ"* አላቸው (1 ነገ.18፥21)። ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ *"እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድ ላይ ማገልገል አይቻልም"* በማለት ይህን እውነት ገልጦላቸዋል (ማቴ. 6፥ 22)። ጣዖት ስንል ጉልበታችንን፣ መላው ሕይወታችንን፣ መሰጠታችንን ሙሉ በሙሉ የያዙት፣ በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉን ነገሮች ሲኖሩ ነው። ሥጋዊ ፍላጎቶቻችንም፣ "እነርሱን ካላገኘን መኖር አንችልም" ከሚል ደረጃ የሚያደርሱን ነገሮች መልካም የሚመስሉ ነገሮች እንኳን ጣዖቶቻችን ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በቆለሰያስ 3 ቁጥር 5 ላይ *"ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤ እነዚህም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጎምጀት ናቸው"* በማለት የሚመክረን። ጣዖቶቻችን ሥልጣን፣ ዝና፣ ደስታና እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

የሕይወታችን ዋና ዓላማ ከላይ የጠቀስናቸውን ነገሮች ለማግኘት ከሆነ፣ ያለንን ጉልበታችንን፣ ጊዜያችንን የሚሻሙብን ከሆነ፣ ልባችን ወደ ጣዖት አምልኮት እያመራ መሆኑን ማወቅ አለብን። እነዚህ ጣዖቶች ሕይወታችንን የሚነኩት ምን ያህል ይሆን? ዘማሪው፣ *"የአሕዛብ ጣዖታት ከብርና ከወርቅ የተሠሩ፣ የሰው እጅ ያበጃቸው ናቸው። አፍ አላቸው አይናገሩም፤ ዐይን አላቸው አያዩም፤ ጆሮ አላቸው አይሰሙም፤ ባፋቸውም እስትንፋስ የለም፤ እነዚህን የሚያበጁ፣ የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ"* ይላል (መዝ. 135፥15-18)። ዘማሪው "እንደ እነርሱ ይሁኑ" ሲል፣ እነዚህን ጣዖታት የሚያመልኩ ሰዎች እንደ እነርሱ ሕይወት የሌላቸው ይሁኑ ማለቱ ነው። ይህንን ሐሳብ በኤርሚያስ አማካኝነት እግዚአብሔር *"...አባቶቻችሁ ከእኔ የራቁት ከንቱ ነገርን የተከተሉት ራሳ*

ቸውም ከንቱ የሆኑት ምን ጥፋት አግኝተውብኝ ነው?" ብሎ ይጠይቃል
(ኤር. 2፥5)። በአጭሩ እነዚህን ሕይወት የሌላቸው ጣዖታትን ስናመልክ
እንደ እነርሱ ሕይወት የሌለን እንሆናለን ማለቱ ነው። ሰማያዊው አባታ
ችን በሕይወታችን ከፍተኛ ሥፍራ የሰጠናቸው፣ በመጨረሻው ቀን ኪሣራ
ውስጥ እንደሚጥሉን ዘለቄታነት እንደሌላቸው፣ በእጃችን ልንጨብጣ
ቸው የማንችላቸው፣ ፈጽሞ ዋጋ የሌላቸው መሆናቸውን እንገነዘባለን።
እነዚህ ጣዖታት ሕይወታችንን ብኩን ያደርጉታል። እግዚአብሔር ከማይ
ፈልገው ሥፍራ እየገፉ ይወስዱናል። እንደ ሸንኮራ እገዳ መጥጠው
ከጨረሱን በኋላ ዋጋ እንደሌለው ነገር ከአፋቸው አውጥተው ይተፉናል።
እነዚህ ጣዖታት እግር አላቸው፣ ግን ስንፈልጋቸው ወደ እኛ መምጣት
አይችሉም። እጆች አሏቸው፣ ግን በትግል ውስጥ ስንሆን፣ የእርዳታ እጆ
ቻቸውን ወደ እኛ መዘርጋት አይችሉም። ዐይኖች አሏቸው፤ ግን በልባ
ችን ውስጥ የሚላወሰውን ነገር ያስከፋንና ያሳዘነን ነገር ማየት አይች
ሉም። ጆሮ አላቸው፤ ግን ጩኸታችንን መስማት አይችሉም። ብቸኞች
ስንሆን፣ ውስጣችን በፍርሃት ሲሞላ፣ አጠገባችን ሆነው ሊያጽናኑን፣ ብቸ
ኛነታችንን ሊያጠፉልን አይችሉም።

የዓለም ጣዖታት ሰውን ያሞኛሉ። እውነት ያልሆነውን ተስፋ በመስ
ጠት ስሜታችንን ይቀሰቅሳሉ፤ ያባብሉናል፤ እውነትነት የሌለውን ህልም
ያሳዩናል። ጠጋ ብለን ስናያቸው፣ የሚጨበጥ ነገር የሌላቸው ናቸው።
"ጊዜህንና ራስህን ብትሰጥ፣ አንተ በምትፈልገው መንገድ ቀርጸን የምትፈ
ልገው ዓይነት መሆን እንድትችል እናደርግሃለን" ይሉናል። ይበሉን
እንጂ ተስፋ የገቡልንን ነገር ሊፈጽሙልን የሚያስችል ኃይል የላቸውም።
በልባችን ውስጥ ሊታተም የሚገባው ምስል (ቅርጽ) ቢኖር፣ የኢየሱስ
ክርስቶስ ብቻ ነው። የበጎ ነገር ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ብቻ ነው።
እርሱን ስንፈልግና ስናገኘው ከእርሱ በሚፈልቁ በጎ ነገሮች የተሞላን
እንሆናለን። ሌላው ቀርቶ እርሱንም እንመስላለን። ዮሐንስም ይህን እው
ነት በአንደኛው መልዕክቱ ያረጋግጥልናል። "ወዳጆቼ ሆይ! እኛ አሁን የእ
ግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፤
እርሱ በተገለጠበት ጊዜ እናየዋለን፤ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን"
ይላል (1 ዮሐ. 3፥2)። በመጨረሻው ቀን በሕይወታችን ዘመን ሁሉ የለፋ
ንበት፣ ለክርስቶስ መንግሥት ስንል የደከምነው ድካም ሁሉ መቶ ዕጥፍ
አፍርቶ እናገኘዋለን። ያገኘነው ትርፍ፣ ያፈራነው ፍሬ ሁሉ ሳይበሰብስና



ሳይጠፋ እናገኘዋለን። ታዲያ የማይጨበጠውን ጥላ ለምን እናሳድዳለን?
ጌታን ትተን ለምን ጣዖታትን እናመልካለን? ለምን ጥየታትን እናገለግላ
ለን? ልባችን መሸከም (መያዝ) የሚችለው አንድ ጌታ፣ አንድ አምላክ
ብቻ ነው። ሁለት ጌቶች፣ ሁለት አምላኮች መያዝ አይችልም። በልባችን
ሥፍራ የምንሰጠው፣ በልባችን ውስጥ የምናገለግለው ጌታ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ብቻ ለምን አይሆንም?

እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጧ ያለውን የመፍጠር ሥራውን ሲፈ
ጽም፣ "ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ" አለ (ዘፍ. 1፥26)። በከ
ፍታውም፣ በዝቅታውም፣ በደስታውም ሆነ በሀዘንም የእግዚአብሔር ፍላ
ጎት አንድ ነገር ነው። ያም በየቀኑ፣ በየሰዓቱ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን
እንድንመስል መቅረጽ ነው። ጳውሎስ "እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸ
ውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ፣ አስቀድሞ ወሰናቸው" ይላል (ሮሜ
8፥29)። በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ሥር የምንኖርና በእርሱ የምንታ
መን በመጨረሻው ቀን የእርሱን መልክና ውበት እንይዛለን። ጳውሎስ
"የምድራዊውን ሰው መልክ እንደለበስን፣ የሰማያዊውን ሰው መልክ ደግሞ
እንለብሳለን" ይላል (1 ቆሮ. 15፥49)። እግዚአብሔር በሕይወታችን እር
ሱን እንድናስቀድም የሚጠይቀን ጥሩ ምክንያት ኖሮት ነው። ምክንያ
ቱም እንደ ንጋት ኮከብ የደመቀውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመ
ስል ስለሚፈልግ ነው። የእርሱ ፍቅር ከዚህ ክፉ ዓለም አውጥቶ ልዩ መል
ክና ውበት ሊሰጠን የሚችል ኃይል እንዳለው ይውቃል። ስለዚህ ጳውሎስ
"...በአዕምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" በማለት
ይመክረናል (ሮሜ 12፥2)።

መብልና መጠጥ፣ የሩካቤ ሥጋ ፍላጎት የሰውን ልጅ ምን ያህል
እንደሚገዙት፣ በተቃራኒ መንገድ ሊሰዱት እንደሚችሉ የታወቀ ነው።
እግዚአብሔር ከደነገገው ውጪ፣ ከጋብቻ ክልል ውጪ የሩካቤ ሥጋ
ግንኙነት ለሰው ልጅ ጣዖቱ ሊሆን እንደሚችል የታወቀ ነው። ለዚህ ነው
ሐዋርያው ጳውሎስ "ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤ ይሁን እንጂ፣ ሁሉም ነገር
አይጠቅምም፤ ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤ ይሁን እንጂ፣ ምንም ነገር በእኔ
ላይ አይሰለጥንም። ደግሞም ምግብ ለሆድ ነው፤ ሆድም ለምግብ ነው፤
እግዚአብሔር ግን ሁለቱንም ያጠፋቸዋል። ሰውነት ለጌታ ነው እንጂ ለዝ
ሙት አይደለም፤ ጌታም ለሰውነት ነው" ያለው (1 ቆሮ. 6፥12-13)።

# እግዚአብሔር ለምን ይቀናል?

"...እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ..." የሚለውን ሐሳብ ስንሰማ፣ "ቅናትን" ሁልጊዜ የምንመለከተው እንደ ክፉ ነገር ስለሆነ፣ "ፍጹምና ቅዱስ አምላክ ሆኖ እንዴት እግዚአብሔር ይቀናል?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እግዚአብሔር "እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ" ሲል፣ ፍቅሩን እንጂ ጥላቻውን የሚያሳይ አይደለም። ሚስቱን የሚወድ ባል በሚስቱ እንደሚቀናው ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ሕዝቡን በጣም ስለሚወድ፣ ሌላ እምላክ ሲያመልኩ ይቀናል። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቅናት ሰው የሚቀናውን ዓይነት ቅናት አይደለም። ሰው የሚቀናበት የራሱ የሆነ ትክክል ያልሆነ ምክንያት ሊኖረው ይችላል። ሰው በራሱ እምነት ሲያጣ፣ የዝቅተኛነት ስሜት ሲሰማው፣ ያለምክንያት እንዲሁ በቅናት ሊሞላ ይችላል። የእግዚአብሔር ቅናት ግን እናት ለልጆቿ በጎ ነገር እንደምትመኘውና እንደምትቀናው ዓይነት ነው። እግዚአብሔር በጣም ስለሚወደን፣ ከእርሱ ፈቃድ ውጪ ብንኖር እንደምንጎዳ ስለሚያውቅ፣ ሁሉ ነገር በጎ እንዲሆንልን ስለሚፈልግ፣ ሕጉን መጣሳችንን አይወድም። ሚስቱን የማይወድ ባል፣ ከእርሱ ሌላ ሌሎች ወንዶች ብትወድ ግድ ስለማይኖረው የቅናት ስሜት በውስጡ እንደማይኖር የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ግን እኔና እናንተን በጣም ስለሚወደን፣ ከእርሱ ሌላ አምላክ ስንወድ፣ ወይም ሁለቱንም ለመያዝ ስንሞክር እግዚአብሔር ይቀናል።

በትዳር ላይ ለረጅም ዘመን የቆየ ሰው፣ አንድ ቀን የአንዲት ቆንጆ ሴት ፎቶግራፍ መስታወት ውስጥ አስገብቶ መኝታ ቤቱ ግድግዳ ላይ ቢያንጠለጥል፣ በቃል ኪዳን ያገባት ሚስቱ የዚህችን ሴት ፎቶግራፍ መኝታ ቤቷ ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ብታይ ምን ይሰማት ይሆን? ዝም ብላ ታልፈዋለች? አይመስለኝም። ባሏን "ይህቺ ሴት ማን ነች?" ብላ መጠየቋ አይቀርም። ባሏም ስሟን ጠርቶ "እከሊት ትባላለች። ከአወቅኋት ይሆን ያህል ጊዜ ሆኗል። አንዳንዴ ፍቅር ሲርበኝና ሲጠማኝ ፍቅር የምትሰጠኝ፣ ኑሮን ለመግፋት ጉልበት ሳጣ የምታነቃቃኝና የምታደፋፍረኝ፣ በጣም የምወዳት ፍቅረኛዬ ነች" ቢላት ፈገግ ብላ "እንዴት ቆንጆዬ ሴት ነች!" ብላ የምታልፈው ይመስላችኋል? አይመስለኝም። በንዴትና በቁጣ ተሞልታ፣ ፎቶግራፉ ከተንጠለጠለበት አንስታ መሬት ላይ ወርውራ መስታወ



ቱን ሰብርብር አድርጋ፣ የሴትዮዋን ፎቶግራፍ በጫጭቃ እንደምትጥል እርግጠኞች ነን። ይህን በማድረጓ ለመሆኑ ይፈረድባት ይሆን? አይመስለኝም። በቃል ኪዳን ያገባችው ባሏ ስለሆነ የባሏን ፍቅር የተሻማችውን ሴት ፎቶግራፍ በጫጭቃ ብትጥል፣ በባሏ ላይ ብትቆጣ ሙሉ መብት አላት ብለን እናምናለን። ምክንያቱም ሚስቱ አድርጎ በቃል ኪዳን ሲያገባት፣ ፍቅሩን ለሚስቱ ብቻ እንዲሰጥ እንጂ ለሌላ ሴት እንዲያካፍል አይደለም። በዚህ ዓይነት ይህቺ ሴት ብትቀና "ቀናተኛ" ተብላ አትነቀፍም።

እግዚአብሔርም "እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ" የሚለውን ቃል ሲያሰማን፣ ለእኛ ያለውን ፍቅሩን እንጂ፣ በተቃራኒ ሁኔታ አናየውም። የተሳሳተ እርምጃ ወስደን ክፉ ነገር ላይ እንዳንወድቅ ሁልጊዜ ዓይኖቹ በእኛ ላይ ናቸው። በዓይኖቹ የሚጠብቀን ስህተት ስንሠራ እጅ ከፍንጅ ሊይዘን ሳይሆን፣ ለእኛ በጎ የሆነውን ነገር ስለሚያስብልን ነው። ልጇን የምትወድ እናት ልጇ ውጪ ወጥቶ ሲጫወት ዓይኖቿ ከልጇ ዓይን ላይ አይነሱም። ይህን የምታደርገው በጨዋታው ላይ ደስ እንዳይለው ለማድረግ ሳይሆን፣ በመንደራቸው የሚያልፈው መኪና እንዳይገጨው፣ አንዳንድ ወንበዴዎች ይዘውት እንዳይጠፉ ልጇን ለመጠበቅ ነው። ልክ እንደዚሁ የእግዚአብሔርም ዓይኖች ሁልጊዜ በእኛ ላይ ናቸው። በዓለም ላይ ብዙ መንፈሳዊ ወንበዴዎች (የጨለማ ኃይሎች) ልባችንን ጠልፈው ለመውሰድ የሚጥሩ፣ ጉዳት የሚያደርሱብን፣ ሰብርብራችንን ካወጡን በኋላ እንደ ቆሻሻ ዕቃ ሊጥሉን የሚፈልጉ አሉ። እናት ለምትወዳቸው ልጆቿ እንደምትቀናው እግዚአብሔርም ስለ እኛ ደህንነትና በጎነት በጣም ይቀናል።

አጥፊያችን የሆነ እንግዳ ነገር ሲያባብለን፣ እግዚአብሔር ይቀናል። ልባችን ወደሚያብለጨልጭ፣ ዓይን ወደሚማርክ ጣዖት ተስበን ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ለመወሰን መቃረባችንን ያያል። ልንሄድበት ልባችን የከጀለበት መንገድ መጨረሻው የጥፋት መንገድ እንደሆነ፣ ለእኛ ብቻ ሳይሆን፣ የልጅ ልጆቻችንም መጥፊያ እንደሚሆን አስቀድሞ የሚታየውና የሚያውቀው ጌታ በምንወስደው እርምጃ እግዚአብሔር ስለ እኛ ይቀናል። ደስታ እናገኝበታለን በማለት የምንወስደው እርምጃችን፣ ውሳኔያችንና ሀሳባችን ትክክል ካልሆኑ የሚወደንን ጌታ ያሳስበዋል። በሚያብለጨልጭ ነገር፣ ዓይናችንንና ልባችንን በሚስብ ነገር እንዳንታለል፣ መጨረሻ ላይ ጣዖት ሲሆንብንና ሲያጠፋን እንደሚችል የሚያውቀው ጌታ ከእርሱ ጋር የሚያራርቀንን ነገር ስናደርግ ሲያይ እናት ለልጇ እንደምትቀናው እር

ሉም ስለ እኛ ይቀናል። ጳውሎስም ሲያስጠነቅቀን "እንግዲህ ጥበብ እንደ ሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ። ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን በሚገባ ዋጁ። ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ" ይለናል (ኤፌ. 5፥15-17)።

ደስታን፣ ዝናን በመፈለግ፣ ጊዜያዊ የሆኑትን፣ ቁሳቁሳዊ ነገሮችን በማሳደድ የተሯሯጡትን፣ የተለያዩ ውሳኔዎችን በሕይወታቸው የወሰኑ፣ መጨረሻው ላይ ግን ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ፣ ራሳቸውን አደጋ ላይ የጣሉትን ስንቶቹን እናውቅ ይሆን? መጨረሻ ላይ ሮጠው ሮጠው የሚፈልጉትን ማግኘት አቅቷቸው፣ ከዚህ በኋላ የትም መድረስ አልችልም በማለት ተስፋ የቆረጡ ስንቶቹን እናውቃለን? ደረስንበት፣ ያዝነው ብለው ሲያስቡ ዳመና መጨበጥ የሆነባቸው፣ ሌላውን ቀደምን፣ ከሌላው በለጥን ብለው ሲያስቡ፣ መጀመሪያ ከነበራቸው ደስታ ያነሰ በማግኘታቸው ተበሳጭተው ራሳቸውን የገደሉትን ስንቶቹ እንደሆኑ እናውቅ ይሆን? በግል ባናውቃቸውም ታሪካቸውን በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች ሰምተናል። የለፉለትና የተሯሯጡለትን ያህል፣ የዚህን ዓለም ኑሮ ኖረው ገና ሳይጠግቡት፣ በወጣትነት ዕድሜያቸው፣ "ከዚህ በኋላ መኖር አቃተኝ" በማለት ራሳቸውን የገደሉ ጥቂቶች አይደሉም። እንዳሰቡት በለመለመ መስክ አላረፉም፤ ወደ ዕረፍት ውሃ አልደረሱም፤ በጽድቅ መንገድም አልሄዱም፤ መንፈሳቸውም አልታደሰም።

ዓለም የራሱን ቅርጽ እንዳያወጣልን ሐዋርያው ጳውሎስ "እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱት" በማለት ይመክረናል (ኤፌ 4፥24)። ዓለም የሚሰጠውን ለመቀበል ብዙዎች በጣም ከፍተኛ ዋጋ እየከፈሉ ናቸው። እግዚአብሔር በነጻ የሚሰጠንን ብዙዎች ብዙ ዋጋ እየከፈሉበት ነው። በነጻ የምናገኝበትን መንገድ ጌታ ኢየሱስ ሲገልጽልን፣ "ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመርላችኋል" ይላል (ማቴ. 6፥33)። ዓለም "ሀብት (ብልጽግና)፣ ሥልጣን፣ ደስታን ፈልጉ" ሲለን፣ እግዚአብሔር ግን እኔን አስቀድሙ (አንደኛ አድርጉኝ) ይለናል።

የምንኖረው እግዚአብሔርን ከሕይወታቸው ፈጽሞ ካስወጡት፣ በምትኩ ግን እንዳያመልኩ የከለከላቸውን ጣዖታት በሚያመልኩ ትውልድ ዘመን ነው። በእግዚአብሔር ምትክ የተቀበሉት ጣዖታት ሕይወት የሚሰጧቸው ሳይሆኑ ብዙ ዋጋ የሚያስከፍሏቸው ናቸው። "ለእኛ ብትሰግድልን፣ ብታመልከን ደስታን እንሰጥሃለን" ይሉታል። እግዚአብሔር ግን "ለራስህ ምንም ዓይነት ጣዖት አታብጅ፣ አትስገድላቸውም፤ አታምልካቸውም... ምክንያቱም ባላሰብከው ሰዓት ልብህ እንዳይሰበር... እምቢ ብለህ በራስህ ፈቃድ ከሄድክ ግን ከውስጥህ ሊነቀል የማይችል ሀዘንና ጸጸት ይደርስብሃል" ይለናል። እግዚአብሔር ወደ እርሱ ተጠግተን የሕይወትን ንጹሀና ቀዝቃዛ፣ ጥማችንን የሚያረካ የሕይወት ውሃ ሊሰጠን ሲጠራን፣ እምቢ ብለን ውሃ ሊሰጠን የማይችለውን፣ የራሳችንን የውሃ ጉድጓድ ለመቆፈር ስንታገል ማየት እንዴት ያሳዝናል? ዓለም ምንም ዓይነት ተስፋ ቢሰጠን፣ ከእርሱ የምናገኘው ነገር የበለጠ እንድንጠማ ያደርገናል እንጂ፣ ጥማችንን ሊያረካ እንደማይችል እናውቃለን። በኤርምያስ አማካኝነት እግዚአብሔር "ሕዝቤ ሁለት ኃጢአት ፈጽመዋል፤ ሕያው የውሃ ምንጭ የሆንሁትን እኔን ትተዋል፤ ውሃ መያዝ የማይችሉትን ቀዳዳ የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል" ይላል (ኤር. 2፥13)።

እግዚአብሔር በየቀኑ ያልደፈረሰ ንጹሕ ውሃ፣ ምንም ሳንለፋና ሳንከፍል እንዲሁ በነጻ ሊሰጠን ሲጠራን እምቢ ብለን ውሃ መያዝ የማይችሉትን የውሃ ጉድጓድ ለራሳችን ስንቆፍር ሲያይ እግዚአብሔርን ምን ያህል ያሳዝነው ይሆን? ጥማችንን ያረካል፣ ፍላጎታችንን ያሟላል ብለን ያሰብነውና የለፋንበት፣ በጣም በሚያስፈልገን ጊዜ ምንም ዓይነት ዕርካታ የማናገኝበት ደረቅ፣ ውሃ የሌለበት ጉድጓድ ሲሆንብን ልባችን በሀዘን እንደሚሰበር የታወቀ ነው። ኃጢአት ከባድ ሥራ ነው። ድንጋይ ቆፍሮ ወይም ፈልጦ ውሃ ማውጣት ዋጋ የሌለውና የሚያሳዝን ልፋት ነው። መጨረሻውም ላይ እንደጠበቅነው ሆኖ አናገኘውም። ፈጽሞ ውሃ መያዝ የማይችል ነው። ሕያው የውሃ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን ትተው ፊታቸውን ወደ ጣዖታት የሚመልሱ ሰዎች የሚያገኙት ጥማቸውን ሊያረካላቸው የሚችለውን ንጹሁ ውሃ ሳይሆን ጭቃ፣ አሸዋ የሚሸት ነገር ያለበትን ደረቅ ጉድጓድ ብቻ ነው። ደስታን እናገኝበታለን ብለው ፊታቸውን ወደ ብልጽግና (ሀብት)፣ ዝናና ክብር የሚያዞሩ፣ በእግዚአብሔር ብቻ ተስፋ ማድረግ ሲገባቸው ከላይ በዘረዘርናቸው ነገሮች ላይ ተስፋቸውን ካደረጉ፣ ውሃ መያዝ የማይችሉትን ቀዳዳ የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶችን ለራሳችን መቆፈራችን ይሆናል።

